ትምህርተ ሃይማኖት መማሪያ



የባህርዳር ፈለገ ገ/ቅ/ጊዮርጊስ ሰ/ት/ቤት ትምህርት ክፍል ተዘጋጀ።

ግንቦት 2007 ዓ.ም

ባሕር ዳር

ምሥጋና፤

በባ/ዳር ፈ/ገ/ቅ/ጊዮርጊስ ካቴድራል ሰ/ት/ቤት ተከታታይ የቤተክርስቲያን ትምህርት እንዲሰጥ ከማሳሰብ ጀምሮ ዛሬ የማስተማሪያ ማንዋል ተዘጋጅቶ ለህትመት እስኪበቃ ድረስ በተለያዩ ወንድሞችና እህቶች ልቦና አድሮ ሥራዉን ከዚህ ላደረሰ የእስራኤል አምላክ ክብር ምስጋና ይግባዉ አሜን።

እግዚአብሔር የሰጠህን መልሰህ በመስጠት ገንዘብህ እንዲባረክልህ አዉቀህ እና ተረድተህ በ47ኛ ዓመታዊ በአል አከባበራችን ወቅት የገጠመንን የህትመት ችግር ለወላጆቻችን በሪፖርት ባቀረብን ጊዜ፤ ሙሉዉን ህትመት በነጻ አትሚ አቀርብላችኋለሁ በማለት ቃል በመግባት በቃልህ ለተገኘኸዉ የቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት ባለቤት ለሆንከዉ ለወንድም ገ/ጻድቅ.. ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በቃልኪዳኑ ይጠብቅልን አሜን።

ደግሞም በተለያዩ መ/ቤቶች በጽህፈት ሥራ ተቀጥራችሁ ለምትሰሩ እህቶች ረቂቁን በመጻፍ በኩል ላደረጋችሁልን አስተዋጽኦ እንዲሁም በሰ/ት/ቤቱ ዉስጥ በማስተማር አገልግሎት ላይ ለምትገኙ መንፈሳዊያን ወንድሞች ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትሉ ለከፈላችሁት የዕዉቀት፣የገንዘብና የጊዜ መስዋዕትነት እግዚአብሔር አምላክ የድካም ዋጋችሁን በሰማይ ያቆያችሁ አሜን።

የካቴድራሉ ሰ/ት/ቤት

<u>ቀዳሚ ማስታወሻ፤</u>
<u>ለመላ ኢትዮጵያዊያን፤</u>

‹‹ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።››
የይሁዳ መልእክት 1፣3

በሃይማኖት የማይገኝ ነገር የለም። ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዚህ እንግዳ አይደለችም። ከአለም አህጉራት በፊት እግዚአብሔርን የሚያዉቁ፣ እግዚአብሔርም የሚያዉቃቸዉ ሀገር ፣ ከነ ሐብቷ፣ ከነ ክብሯ፣ ሃይማኖት ከነ ሥርዐቱ ቋንቋ ከነ ፊደሉ፣ከነ ሥነ ጽሕፈቱ፣ አስተዳደር ከነህጉ ከነ መብቱ አሟልቶ የሰጣቸዉ አባቶች ነበሯችሁ ። በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 7;14 ‹‹ትርንጎዎች መዓዛን ሰጡ መልካሞች ፍሬዎች ሁሉ፥ አሮጌው ከአዲሱ ጋር፥ በደጃችን አሉ ›› እንዳለዉ በመንፈሳዊዉም ፤በሥጋዊዉም ብሉይ ከሐዲስ የተሟላላት ሀገር ነበረችን። ዛሬ ግን ሁሉም እየታጣ ነዉ። ኢትዮጵያ የገነት ጎረቤት እንደመሆንዋ (ዘፍ.2፤13) በገነት ያለ ሐብት ሁሉ በኢትዮጵያ አለ። ግን የሚወረሰዉ በሃይማኖት ስለሆነ ሃይማኖት ከሌለ ሁሉም የለም። ስለዚህ ሁሉን አጥቶ ከመቸገር ፣ ሁሉን ላለማጣት ሃይማኖትን ማግኘት። ነባራቱን ሃይማኖታችን አጥብቀን እንያዝ፤ያኔ ሁሉም የእኛ ይሆናል። እምቢ ብንል ፍርድ ይጠብቀናል። ወደ እግዚአብሔር እንመለስ ይመለስልናል። ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ ፣ እርሱም ወደ እኛ ይቀርባል፣ ይህንን አደራ በፍቅር እንድትቀበሉኝ በእግዚአብሄር ስም እማጸናችኋለሁ።

አለቃ አያሌዉ ታምሩ

የቀድሞዉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲን
የሊቃዉንት ጉባኤ ሰብሳቢ
ዕርቅ ሰላምና ምልጃ ከሚለዉ መጽሐፍ
የተወሰደ

መግቢያ፤

የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ ለመንፈሳዊ ትምህርት አዲስ የሆኑ ክርስቲያኖች ለመማር ሲመጡ ወደ ዋናው የሃይማኖት ትምህርት ከመግባታቸው በፊት እነርሱን በሚመጥን መልኩ የተዘጋጀ የመግቢያ ትምህርት ነው።

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት መማራቸው ቀጣዩን የትምህርተ ሃይማኖት ክፍል ለመማር የቀና ይሆንላቸዋል። ከዚህም ባሻገር ትምህርቱን ጀምረው እንዳያቋርጡ የመንፈሳዊ ሕይወትን ጥቅም በአግባቡ ተረድተው ቀጣይ የህይወት

መንገዳቸው ምን መሆን እንዳለበት እንዲወስኑና ጨክነው ጊዜያቸውን በመስጠት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ግንዛቤ የሚጨብጡበት የትምህርት ክፍል ነዉ።

ክርስቲያኖች ይህንን የትምህርት ማንዋል በትምህርቱ ወቅት በአግባቡ እያነበቡና ያልገባቸዉን እየጠየቁ ሊጠቀሙበት ይገባል እንጅ ማንዋሉን ገዝቶ በእጅ ማድረግ ብቻዉን በህይወት ለመለወጥ ፋይዳ አይኖረዉም።

በመጨረሻም ተማሪዎች ይህንን የተማሩትን ትምህርት በሚሄዱበት ስፍራ ሁሉ ለሌሎች ወገኖቻቸዉ በማካፈል ክርስቲያናዊ ግዴታቸዉን ሊወጡ ይገባል።

ሰንበት ት/ቤቱ

ማዉጫ፤

መግቢያ፤ 3

1. ሃይማኖት 5

1.2 ከክርስትና ዉጭ የሆኑ የክህደት አስተምህሮዎች፤ 7

1.3.አንዲቷ ቤተክርስቲያን መቸ ተከፈለች? 7

1.4 የተሐድሶ ፕሮቴስታንት በኢትዮጵያ፤ 9

1.5 የሃይማኖት /የእምነት ተቋማት ሲያሚዎች ትርጉም 9

1.6 ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ክፍፍል ሥዕላዊ መግለጫ፤ 11

2. ክርስቲያንና ጥሪዉ፤ 12

4. የእግዚአብሔር ህልውና 23

4.2. የእግዚአብሔርን ህላዌ የሚያመለክቱ ባህርዮች፤ 25

5. የክርስትና ትምህርት ምንጭ/መነሻ 28

6. ሥነ ፍጥረት፤ 31

የሰው አፈጣጠር፤ 32

የመላእክት አፈጣጠር 33

የሰይጣን ዉድቀት፤ 34

ክፍል 1

1.ሃይማኖት

ሃይማኖት በዓይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ በጆሮ ብቻ ሰምቶ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ሳይሉ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል ብሎ በህሊና አምነዉ የሚቀበሉት ረቂቅ ምስጢር ሲሆን በዉስጡም አምስት አእማድ አሉት።

1.1 የሃይማኖት መነሻውና ምንጩ

ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ነው። ሃይማኖት ማለት ማመን መታመን ማለት ነዉ። የምናምነዉም የዓለሙ ሁሉ ፈጣሪ የሆነዉን የሰማይና የምድር ንጉስ ልዑል እግዚአብሔርን ሲሆን ለዚህ ላመንነዉ አምላክ ታምነን ታማኝነታችንንም በተግባር ማሳየት ስንችል ሃይማኖተኛ እንባላለን ፤ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ ማለትም ይቻላል፤ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 4፣7 ‹‹መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ ሩጫውን ጨርሼአለሁ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ››፤እንዳለ ቅዱስ ጳዉሎስ፤

በአጠቃላይ እንደ ቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ የሃይማኖት ምንነት የሚገለጠዉ በአምስቱ አዕማደ ምስጢራት አማካኝነት ነዉ። ከእነዚህ ምስጢራት መካከል አንዱን የማይቀበል ቢኖር ሃይማኖትና የመዳን ተስፋ የሌለዉ ነዉ።ምክንያቱም ሥላሴን ያላመነ እግዚአብሔርን አያዉቀዉምና፤ሥጋዌን ያላመነ ክርስቶስን ክዶአልና (ዮሐ.6፤47)፤ ያልተጠመቀ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባምና (ዮሐ.3፤8)፤ ሥጋዉን ያልበላ ደሙን

ያልጠጣ /ያልቀረበ/ የዘለዓለም ህይወት የለዉምና (ዮሐ.6፤54)፤ ትንሳኤ ሙታንን ያልተቀበለ የክርስቶስን ትንሳኤ ክዶአልና (1ኛ ቆሮ.15፤17)።-

ሃይማኖትም አንዲት ናት፤ ምክንያቱም የምናምነዉም ሆነ የምንታመነዉ ለአንድ አምላክ ለአንድ እዉነት ነዉና። ድህነት የምናገኝበት የእምነት መንገድ ደግሞ አንድ ነው እንጂ ከአንድ በላይ ሊሆን አይችልም። ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አንድ ነው እግዚአብሔር ደግሞ እውነት ነው ።እውነትም አንድ ነው ስለዚህ ሃይማኖት አንድ ነው ።

‹‹ አንድ ጌታ ፤አንድ ጥምቀት፤አንድ ሃይማኖት›› ኤፌ.4፤5 የሚለውን የሐዋርያውን ቃል መሠረት አድርገን ስንነጋገር አንድ ሃይማኖት የተባለበት ምክንያት ጌታ አንድ ስለሆነ ብቻ ነው። ከአንድ በላይ ጌታ ቢኖር ከአንድ በላይ ሃይማኖት አለ ባልን ነበር።

ዛሬ በዓለማችን ከ30ሺህ በላይ በክርስትና ስም ያሉ እምነቶች ሁሉም ወደ ዘለዓለም ሕይወት አያደርሱም፤ ከአንዱ በቀር ሁሉም ወደ ሞት እንጂ ወደ ሕይወት አያደርሱም እውነቱ አንድ ብቻ ነውና።

ሃይማኖት ያድናል?

መልሱ አዎ ያድናል ነዉ። በ2ኛ ጢሞቴዎስ 4:7 ‹‹መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ››፤እንዳለ ቅዱስ ጳዉሎስ። ሃይማኖት እውነተኛዋና አንዲቱ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምታደርሰው የትኛዋ እንደሆነች ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከታሪክ አንጻር መፈለግ የሁሉም ድርሻ ነዉ። በእውነተኛዋ ሃይማኖት ውስጥ አስተምህሮዋን ተከትሎ መኖር ያድናል። ተግባሯን ሳይፈጽሙ ኦርቶዶክስ ነኝ ማለት ግን አያድንም።ቅዱስ ጳዉሎስ ተብሎ በስሙ መጠራት የድል አክሊል አያቀዳጅም በአንጻሩ ደግሞ ቅዱስ ጳዉሎስ የተÕዘበትን የህይወት መንገድ ተከትሎ መኖር እንደ ቅዱስ ጳዉሎስ የድል አክሊልን ያቀዳጃል። ስለዚህ መባል ያለበት ‹‹ስም አያድንም›› ነዉ እንጅ ‹‹ሃይማኖት አያድንም›› አይባልም።

<u>ለተጨማሪ ማብራሪያ፤</u>

ሐይማኖት የማያድን ቢሆን ኖሮ አባቶቻችን ከዚህ በታች ያለዉን ቃል ባላስተማሩንም ነበር።-

- 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 16፣**13**‹‹ንቁ ፥ በ**ሃይማኖት** ቁሙ፥ ጎልምሱ ጠንክሩ።።››
- የይሁዳ መልእክት 1፡**3** ‹‹ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ **ሃይማኖት** እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።።››
- 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 5፡**8** ‹‹**ሃይማኖትን** የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።።››
- 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 6፡**10** ‹‹ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከ**ሃይማኖት** ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ››።።
- ትንቢተ ኤርምያስ 6፡**16** ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ።።››

1.2 ከክርስትና ዉጭ የሆኑ የክህደት አስተምህሮዎች፤

1.2.1 የአርዮስ ትምህርት፤

በ257 ዓ.ም በሊቢያ የተወለደዉ አርዮስ ካህንና ታዋቂ መምህር ነበር።ይህ ሰዉ ወልድ ፍጡር ብሎ ቢነሳም ከተለያዩ የዓለም አቅጣጫ የተሰባሰቡት 318 የቤተክርስቲያን ሊቃዉንት በአንድ ድምጽ አዉግዘዉ ለይተዉታል። በዚህም ምንም የመከፋፈል ተጽዕኖ ሳያሳድር አልፏል።

1.2.2 የመሐመድ ትምህርት፤

የእግዚአብሔር ነቢይ ነኝ ብሎ በ570 ዓ.ም ተወልዶ በ632 የሞተው የመካ ተወላጅ የነበረው መሐመድ ክርስቶስን ነቢይ በማለት ተነስቶ ለሠው የሚመች ህግ ሰርቶ ተነሳ። አባቱ መጠነኛ ገቢ የነበርው ነጋዴ ነበር:: ገና በልጅነቱ አባቱ ከአጠገቡ በሞት ሰለተነጠቀ ለአጎቱ የበግ እረኛ ሆኖ ማገልገል ጀመረ:: ዳሩ ግን እሰከ መጨረሻው የበግ እርኛ ሆኖ አልዘለቀም ነበር፤ በእድሜ ከእርሱ ብዙ ለምትርቀው ለሀብታምዋ ነጋዴ ለከድጃ ባል ሆነ:: መሐመድ እንቅሰቃሴውን እንዲጀምር ያነሳሳውን ሁኔታ ራሱ ሲገልጽ አንድ ቀን ከከተማ ውጭ በኮረብታ ላይ ለብቻው ተቀምጦ ሳለ ታላቁ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ነቢይ እንዲሆን እንደተመረጠ መነገሩን ይናገራል ::

ከዚያ ወዲያ በመካ በአዲሱ እምነት ውስጥ መሰበክ ጀመረ:: ዳሩ ግን በዚያ ቅጽበት መካ እሺ በእጄ ብላ በአዲሱ እምነት ልትገባ አልቻለችም እንዲያውም ብዙ ተቃዋሚዎች ተነሱበት። በተለይ ካህናተ ጣኦታት ሕዝቡን ያሳድሙበት ጀመር:: በዚህ ምክንያት የተነሣ የመሐመድን እንቅሥቃሴ የሚደግፉ ወገኖቹ በግመል አስርቀው መዲና ወደተባለች ከተማ ወሰዱት:: ይህም የሆነበት ጊዜ በ 622 ዓ.ም ነበር:: መሐመዳዉያን ዘመናቸውን ከዚህ ጊዜ ጀምረው ነው የሚቆጥሩት ::

1.3.አንዲት ቤተክርስቲያን መቸ ተከፈለች?

ንስጥሮስ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተከለውን የኑፋቄ ሚስማር የታወቀው የተዋህዶ አናጺ ቄርሎስ በተዋህዶ ፋሰ ፈንቅሎ አወጣው፤በንስጥሮስ ክህደት የተሰበሰበዉ ጉባዔም ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባህርይ መሆኑን እመቤታችንም ወላዲተ

አምላክ መሆንዋን መስክሮ ንስጥሮስንና ትምህርቱን አዉግዞ ተበተነ:: የሮም ፤የአንጾኪያ ፤የእስክንድርያና ሌላው የተቀረው የክርስትናው አለም እስከዚህ ቀን ድረስ አንዲት ቤተ ክርስቲያን በሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ይÕዝ ነበር ::

ይሁን እንጂ ይህችን አንዲቱን ቤተ ክርስቲያን የሚከፍል ሃሳብ በ451 ዓ.ም ብቅ አለ::ቤተ ክርስቲያን እስከ መቼውም የማትረሳው የአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ከፋፋይ ፓፓሊዮን በነገሥታቱ በነመርቅያንና በነብርክልያ ታጅቦ ቀረበ:: በቅዱስ ቄርሎስ ተዋህዶአዊ ትምህርት ግብአተ መሬቱ የተፈጸመለትን የንስጥሮስን ክህደት የተቀበረበትን አፈር ምሶ በማውጣት ህይወት ዘርቶበት በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ አቀመው:: የተዋህዶ አርበኞች በአባታችን በቅዱስ ቄርሎስ የተወገዘው ትምህርት ዛሬ ከየት መጣ? መጽሐፍ ቅዱስ ያወገዘውን ይህን ትምህርት በፍጹም አንቀበልም ብለው ከጉባኤው ወጥተው ሄዱ:: የተዋህዶ አርበኛ በመባል የታወቀው ታላቁ ዲዮስቆሮስም አንድ አካል አንድ ባህርይ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በገሃድ መሰከረ ::

ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ እስከ 450 ዓ.ም ድረስ በየጊዜው የተነሱትን የስህተት ትምህርቶች በጉባኤ እያየችና እያረመች የመጣች ቢሆንም በንስጥሮስ የተነሳው የሁለት ባህርይ የክህደት ትምህርት ግን የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ታክሎበት በ451 ዓ.ም በኬልቄዶን ጉባኤ አንዲቱ ቤተክርስቲያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶና ካቶሊክ ተብላ ተከፈለች።

ከዚህ በኋላ በ16ኛው መ/ክ/ዘ ካቶሊክን በማደስ በማርቲን ሉተር በተደረገ የተሐድሶ እንቅስቃሴ ታላቁ የሃይማኖት ክፍፍል በፕሮቴስታንት አራማጁ ሉተር ተጀመረ።

የፕሮቴስታንት እምነት ስሙ እንደሚጠቁመን የተቃውሞ እምነት ስለሆነ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጥገናዊ ለውጥ ያስፈጋታል በማለት ከሐዋርያት ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ወጥቶ ብዙ ነገሮችን ነቀፈ:: እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1517 ዘጠና አምስቱ ዓረፍተ ነገሮች የተባለውን በዊተንበርግ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ በወረቀት አድርጎ ለጠፈ:: በዚህም ምክንያት ከሮም ቤተ ክርስቲያን ማፈንገጡን ይፋ አደረገ ::ከማርቲን ሉተር ስሕተታዊ ትምህርቶች ውስጥ አንዳንዶቹን ብንጠቅስ ፡-

ሀ. ምንኩስና አላስፈላጊ እንዳልሆነና ገዳማትም መዘጋት እንዳለባቸው

ለ . በጽሎት ጊዜ የቅዱሳንን ስም መጥራት እነርሱንም እንደ አማላጆች አድርጎ

መቁጠር ስህተት መሆኑን ፤

ሐ. ማንኛውም ሰው በራሱ አተረ∏ጎም መጽሐፍ ቅዱስን ጸልዮ መረዳትና መተርጎም ይችላል የሚሉት የክህደት አስተምህሮ ለብዙ እምነቶች መፈጠር ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ ነው።

በአሁን ጊዜ እንደ አሸን ለበዙ የእምነት ድርጅቶች መፈጠር ዋና መንስኤ የሆነው ይኸው አባባል እንደሆነ በብዙዎች ይታመናል።

በዚህ ባለንበት ዘመን በክርስትና ስም እን≤ን ከ32 ሺህ በላይ የእምነት ድርጅቶች እንዳሉ ይነገራል ።እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ‹‹አንዲት ሃይማኖት ፤አንዲት ጥምቀት›› ብሎ ስለ አንዲት ሃይማኖት ሰብኮ እያለ ይህ ሁሉ እምነት ታዲያ ሊኖር ይገባ ነበር?

የካቶሊክ እምነት በዚህ የተሐድሶ እንቅስቃሴ ብዙ ሐገራትንና ህዝቦችን በፕሮቴስታንት ብትነጠቅም ባደረገችው የፀረ-ተሐድሶ (Counter Reformation) እንቅስቃሴ የተነጠቀችውን ማስመለስ ባትችልም የተሐድሶውን እንቅስቃሴ ግን ለመግታትና ያሉትን ይዛ ለመቀበል ችላለች፤

ሉተር በጀመረው የፕሮስታንት ተሐድሶ እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ ብዙ መንገድ ሳይጓዝ የፕሮቴስታንት እምነት በአራት ዋናዋና ክፍሎች ተክፍሏል። እነርሱም፡-

1.ሉተራን

2.ካልቪኒዝም (reformed)

3.አናባፕቲስት

4.አንግሊካን ሲሆኑ ክፍፍሉ በአራት ብቻ ሳያቆም በስራቸው ሌሎች ክፍፍሎች በብዛትና በፍጥነት እየተፈጠሩ ሄዱ ዛሬም ክፍፍሉ ሳያቆም አዳዲስ የእምነት ድርጅቶች በመፈጠር ላይ ይገኛሉ ።በሐገራችን እንኳ እንደ ንግድ ፈቃድ በበጉ አድራጉት ድርጅት ስም ፈቃድ እያወጡ እርስ በርሳቸው የሚፎካከሩ ለቁጥር የሚያታክቱ በርካታ የእምነት ድርጅቶች በመፈጠር ላይ ይገኛሉ ።

1.4 የተሐድሶ ፕሮቴስታንት በኢትዮጵያ፤

በርካታ ሰዎች የተሐድሶ እምነት ምንድን ነው? ይላሉ መልሱ አጭር ነው ከላይ እንደ ተመለከትነው የካቶሊክን እምነት ገልብጦ ፕሮቴስታንት ለማድረግ እንደተደረገው የ500 ዓመት ታሪክ ዛሬም አርቶዶክስን ገልብጦ ፕሮቴስታንት ለማድረግ የሚንቀሳቀስ የፕሮቴስታንት ድርጅት ነው፤ስራዉ በፕሮቴስታንት አዝማችነት የሚከናወን ሲሆን በብዙ ስያሜዎች ይንቀሳቀሳል፤ በኢትዮጵያ በየሀገሩ የተለያየ ስያሜ ይዘው ህጋዊ ናቸዉ ለመባል ከመንግስት በበጎ አድራጎት ድርጅ ስም ፈቃድ አወጥተዉ ይንቀሣቀሣሉ ።የሁሉም የተሐድሶ አራማጅ ድርጅት ስም ይለያይ እንጅ በአላማ አንድ ናቸው ።ይfውም የአርቶዶክስን አስተምህሮ ሙሉ በሙሉ በመለወጥ በፕሮቴስታንት አስተምህሮ መተካት ነው ።

ይህ የተሐድሶ ዘመቻ ከዚህ ቀደም ከነበረው ጌታን ተቀበል ከሚለዉ ደረቅ ፕሮቴስታንታዊ ወረራ ልዩ የሚያደርገው በቤተ ክርስቲያን ልሣን ግዕዝ እየተናገሩ በዲያቆናት በቀሳውስት መርጌቶችና በመነኮሣት አማካኝነት የቤተክርስቲያንን አዋልድ መጻሕፍት ባይቀበሏቸውም ለነሱ የሚስማማ ቃል እየመዘዙ በማውጣት የሚናገሩና የሚጽፉ የፕቴስታንት ቅጥር ናቸዉ።

1.5 የሃይማኖት /የእምነት ተቋማት ሲያሚዎች ትርጉም


- **አርቶዶክስ፤-ቀጥተኛ፤ያልተበረዘ ያልተከለሰ ሃይማኖት ማለት ነዉ፤**
- **ካቶሊክ፤-አለማቀፋዊ፤ሁሉ አቀፍ ሃይማኖት የሚል ትርጉም አለዉ**

- **ሉተራን፤-ሲያሚዉን ያገኙት ከፕሮቴስታንት እምነት መስራች ከሆነዉ ሉተር ሲሆን፤ትምህርታቸዉ ሙሉ በሙሉ በሉተር አስተምህሮ ላይ የተመሰረተ ነዉ።**
- **ባፕቲስት/አጥማቂዎች፤- አስተምህሮአቸዉ በጥምቀት አስፈላጊነት ላይ ጠንካራ አቁዋም ያለዉ በመሆኑ ይህ ሲያሚ ተሰጥቶታል።**
- **አንግሊካን፤-የእንግሊዝን የበላይነት ለማረጋገጥ የተመሰረተ ሲሆን ትርጉሙም የኢንግላንድ/የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን ማለት ነዉ።**
- **ሜቶዲስት፤-መንፈሳዊ ህይወትን እንዴት መምራት እንደሚቻል ዘዴን በማፍለቅ የሚታወቀዉ የዕምነቱ መስራች ዮሐንስ ዌስሊ ነዉ፤ ከዚህ በመነሳት ሜቶዲስት ተብሎአል።**
- **ካልቪኒዝም (reformed)፤- ሲያሚዉን ያገኘዉ ከእምነቱ መስራች ከጆን ካልቢን ነዉ።ትምህርቱ የተመሰረተዉም በዚሁ ግለሰብ አስተምህሮ ላይ ነዉ።**

አምስቱ ጥንታዊያን እህት ኦርየንታል (የተዋህዶ) ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲናት ዝርዝር፤

1. **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን**
2. **የእስክንድርያ (የግብጽ፤የኮፕት) ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን**
3. **በደቡብ ህንድ የሐዋርያዉ ቶማስ (የማላባር፤የኬራላ) ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን**
4. **የአርመን (ጎርጎርዮሳዊት) ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን**
5. **የሶርያ (የአንጾኪያ፤ያዕቆባዊት) ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፤ እንኝህ በመሰረታዊዉ የእምነት አስተምህሮ (ዶግማ) እንድ ስለሆኑ አንዱ በአንዱ ቤተክርስቲያን ገብቶ መገልገልም ሆነ ማገልገል ይችላል፤ከአነዚህ ዉስጥ በተከታዮች ብዛት ከፍተኛዉን ቁጥር የያዘችዉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ናት፤**

1.6 ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ክፍፍል ሥዕላዊ መግለጫ፤



↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓

ማቴ. 24፡4-5 ‹‹**ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ**››

2. ክርስቲያንና ጥሪዉ፤

†¿- **ክርስቲያን** lLºWpý ˆ·šê†nHîY**ን** £Më¦µE·E'å ˆ·šê†nHîñY £Mët·T'å D**ኖ** ¨T«èr~ £MëlF& £Mëº»& EˆY\å £Më¦^ÔGµ'å AåEå& EL**ኖ**Y £MëvGlr¿ ˆ¿ª pW \'å **ሊ**¦š¶³Er **አይደለም፤** ¨C lmCY¨'å £EN~¤ mCY¨'å ·¿ mCY**ይዉ**¿ ˆ¦L\µ}'å £Më**ኖ**Y †NFŒ £\'å G³ lN^¶~ †µG·Eør †L^·**ኖ**• ŒnU¿ ¨'Y^ š¿- ÔºT'å::

#N^¶~£¿ ˆ¿«é~µU Eˆ}ï £ÔºYAår ሕœn; †é]. 43□21 ˆ¿«E **ክቢዩ** †é]**ይ**¦^::
£\'å G³ AåEå lp\º'å Ð¶ ¦µE·G š¿- pºW:: ˆ·šê†nHîY '® Ôi® ˆ¿³ ˆƒ ÔGµ¿ & bp¿ & pL„p¿ & º¨d¿ †¨ªEN¤ ˆ¿«éCM ŠD} Ôg«v¿¿ ˆ¿³ Ôg«è¿ †~ªY·N:: NYÁ'å £ˆ·šê†nHîY }'å፤ **ይህ የእግዚአብሔር ጥሪ ደግሞ ለምድራዊ ተድላና ደስታ አይደለም ለሰማያዊ ክብር እንጅ**

- ‹‹**ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥ ››..** ዕብ. 3፤**1 እንዳለ ቅዱስ ጳዉሎስ**
- ...‹‹ **ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።**›› **ኤፌ.** 2:**6-7**
- # †^d-ON £'\~t'å¿ ˆ}šêC¿ ª·O ºWt'å& £ºWt'å¿N ˆ}šêC¿ ª·O †Ðªgt'å:: ¦Ðªgt'å¿ ˆ}šêC¿ ª·O †ŠlWt'å;:: ZMð 8□30:: **እንዳለ እስከ መጨረሻዉ ጥሪያችንን አክብረን ለክብር እንድንበቃ መንገዳችንን ከእግዚአብሔር ጋር ልናደርግ ይገባናል።**

✓ ***<u>በብሉይ ኪዳን ዘመን</u> እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ከተለያየ ሰፍራ ጠርቶአቸዋል፤ ለአብነት ያህልም፦***

- ❖ }ክቢየ ˆ·šê†nHîY i«è^ Lå\î £†Mpý¿ l¸v ŠMëºnilr ŠMð« ŠˆT„}r ECœlå }Ñ L'å»r **ተጠራ** šÐ.3□1፤
  Lå\î¿ Bì-~ EÔY™¿ #¦µE·Eå„ š¿- Cœlî¿ Gdi; lE'å †E µïq ˆ·šê†nHîY:: £\'å G³ AåEå ¦µE·E'å š¿- ¨LY»G**ኖ**:: šÐ 8□1 ˆ~ 10□3
- ❖ ECœlå LV £½Y †Eg EM-T· lÔVB ˆ·šê†nHîY ¦E'å¿ µï«é©¿¿ Š·nY~ ^¿¬¿ ŠMë'glr ºW'å L. L] 6□11

- ECœlå }n¨ ¨D¿Er š¿- d-O †îYN¦^¿ ŠMCÐ¿ E£'å & dª\'å & ºW'å †îY 1□5
- «"ìr¿ £†mstý¿ l¸v ŠMëºnilr £ˆ·šê†nHîY¿ Cœn ¨ºniEr~ £~d'å¿]™G¿ ¨bT'å š¿- Šl· ˆT„}r ECœlå ˆTƒ ¨D¿ š¿- ºW'å 1ኛ ሳሙ.16□11-13
- †OÒ¿N ˆ¿«éAå ŠFN ºmf}r **ጠርቶታል** r¿. †O 1*1

✓ **<u>በሐዲስ ኪዳን</u>፤** lšL} R¶"ò'å ¦µE·Eår š¿- H"Y¦r¿(ªd L›LåYpý¿) ŠpE¦£ oq EšêC EC¨'r †µG·Eør LTº::

- Æï¼Z^¿~ ˆ¿-Y¦^¿ **በገሊላ ባህር አጠገብ** Š—] †¼M³}r ºWt'å ©H 1□፤41-50 ፤ Mpò 4□18
- Mpò•^¿ ŠdWÃ}r **ሥራዉ ጠርቶታል** #lLiTÁ'å pdN½ £}lT'å¿ Mpò•^ £MëmG \'å †£~ pŠpE„ †E'å; Mpò 9□9::
- **ሳዉል ይባል የነበረዉን ጳዉሎሰንም ከክርስቲያን አሳዳጅነቱ ለአገልግሎት ጠርቶታል** ሐዋ.22፤6-18

3 መንፈሳዊነት፤

3.1 በቅድሚያ መንፈስ ማለት ምን ማለት ነዉ?

መንፈስ ማለት በዓይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ ረቂቅ ሐይል ነዉ።

መንፈስ በስንት ይከፈላል?

መንፈስ በሁለት ይከፈላል። 1. **ቅዱስ መንፈስ** 2. **ርኩስ መንፈስ**

1ኛ. ቅዱስ መንፈስ ፤ ይህ የቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን ሰጭዉም ራሱ እግዚአብሔር ነዉ። የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን ወደ እዉነት የሚመራ፤ሁሉን አዋቂ፤የጥበብ ባለቤት፤ እዉነተኛ ፈራጅ በአጠቃላይ መልካምና የመልካም ነገሮች ሁሉ ምንጭ ነዉ፤እርሱን የሚከተልም ሁሉ ይቀደሳል መልካምነትንም ገንዘብ ያደርጋል፤

- **1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች** 2;**12** ‹‹ ... **ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና።**››

ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ ራሱ እግዚአብሔር ነዉ። የእግዚአብሔር መንፈስም አንድ ብቻ ሲሆን ስጦታዉ ግን ልዩ ልዩ ነዉ፡-

- ‹‹ **የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤** ... **ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል** ... **ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል** ... ›› **1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች** 12፤4

2ኛ. ርኩስ መንፈስ ይባላል፤- ይህ የዲየብሎስ (የኢጋንንት) መንፈስ ሲሆን ሐሰትን ፤ ጥላቻን ክፋትን ከራሱ አመንጭቶ በሰዉ ልጆች መካከል የሚዘራ ክፉና የክፉ ነገር ሁሉ ምንጭ ነዉ።

- ‹‹እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። <u>ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና</u>።›› የዮሐንስ ወንጌል 8;**44**
- ‹‹ <u>ክፉው መንፈስ</u> ግን መልሶ፦ ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፤ እናንተሳ እነማን ናችሁ? አላቸው።›› የሐዋርያት ሥራ 19;**15**

3.2 መንፈሳዊዉ ሰዉ ማነዉ?

መንፈሳዊ ሰዉ የምንለዉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነ፤ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚመላለስ በሰዉና በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነ፤ ጻድቅና የመንፈስ ፍሬወች የሚታዩበት ሰዉ ነዉ፤ ስለዚህ ጉዳይ ቅዱስ መጽሐፍ ሲያረዳ እንዲህ ይላል፥-

- ‹‹ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።›› 1ኛ ቆሮ. 6፥**19-20**
- ‹‹የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። ››ወደ ገላትያ ሰዎች 5፤**22**

ይህንን በተግባር ከፈጸሙት መካከል ለአብነት ያህል በመጽሐፍ ቅዱስና በተለያዩ ዘመናት የተነሱ ቅዱሳንን መጥቀስ ይቻላል ፤ ነቢያት፤ ሐዋርያት፤ጻድቃን ሰማዕታትን እንዲሁም የነርሱን መንገድ የተከተሉ ሌሎች ቅዱሳንን መጥቀስ ይቻላል፤

3.4 የአንድ መንፈሳዊ ወጣት መለያ ጠባዮች፤

በቅድሚያ በአብዞኛዉ የ'»r}r ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ እንመልከትå÷

- £ˆNlép„}r šL¿ }'å፤

  ‹‹ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥...›› 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:**2**

- £ˆ]ትና £¿×^ mCርይ £Më\E¼¿lr }'å፤

  አንተ ግን መጽሐፍ እንደተናገረ ∩የጮንቀት ቀን ሳይመጣ በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይደርሱ.....∪መጽሐፈ መክብብ 12□**1** የሚለዉን ቃል ለመፈጸም ትጋ፤

- Or የማይታሰብበት šL¿ ነዉ፤

- አንተ ግን ከሞት በኋላ ስለሚኖርህ ህይወት የሚመጣዉን ቤትህን አስብ ‹‹ አቤቱ፥ እርዳታው ከአንተ ዘንድ የሆነለት፥ በልቡም የላይኛውን መንገድ የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው።››መዝሙረ ዳዊት 84:5
- ∩የጠቢባን ልብ በልቅሶ ቤት ነው የሰነፎች ልብ ግን በደስታ ቤት ነው።∪ መጽሐፈ መክብብ 7□4

አንድ መንፈሳዊ ወጣት ግን የሚከተሉትን ጠባዮች ሊይዝ ይገባል፡-

1. የሚጸልይና የሚጸም
   - የሉቃስ ወንጌል 22:46 ‹‹ ስለ ምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ አላቸው።.››
   - የሉቃስ ወንጌል 18:1 ‹‹.ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፥.››
   - የማቴዎስ ወንጌል 17:21 ‹‹ ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው።.››
2. £Wሱ¿ NYÁ በመተዉ ˆ¿ª ˆ·šé†nHîY ፈg- £ሚጓዝ ፤
   - ኤፌ. 6፡6‹‹ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ።.››
   - ‹‹ እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ።እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም።እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። .›› ሮሜ. 8:5
   - የሐዋርያት ሥራ 21:14 ‹‹ የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን።.››
3. ሕይወቱን በንስሐ የሚመራ
   - የሉቃስ ወንጌል 3:8 ‹‹ እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤.››
   - ‹‹ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።.››ወደ ገላትያ ሰዎች 5:16
4. qM„ £Dነና p^× £M¨jY¼
   - ከቅዱስ ጳዉሎስ ተሰፋ አለመቁረጥን መማር አለብን “...በድካም አብዝቼ፥ በመገረፍ አብዝቼ፥ በመታሰር አትርፌ፥ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ።አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ።ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ።...”2ኛ ቆሮ. 11፤23-25
   - ወደ ሮሜ ሰዎች 8፤24 በተስፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል?”

- ‹‹ባሪያዎች ...ለገዛ ጌቶቻቸው እንዲገዙ በሁሉም ደስ እንዲያሰኙ፥ ሳይቃወሙና ሳይሰርቁም በጎ ታማኝነትን ሁሉ እንዲያሳዩ ምከራቸው።.›› ወደ ቲቶ 2:9-10

5. i዗]r LÎHÙrን የሚያነብ፤
   - 2ƒ °éO 3□16 ∩የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።∪

6. **አሰራቱን የሚያወጣ፤**

ህይወቱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ወጣት ክርስቲያን ለገንዘቡ ሳይሰስት አሰራት የሚያወጣ መሆን ይገባዋል፤ ይህ በመጽሐፍ የታዘዘ ሲሆን የእግዚአብሔርን ገንዘብ ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነዉ።ይኸዉም ከምናገኘዉ ገንዘብ ከአስሩ አንዱ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነዉና፤ይህንን የማያደርግ ደግሞ ገንዘቡ በዚህ ምድር ሲኖር የማይባረክለት ሲሆን እግዚአብሔርንም እንደሰረቀ ይቆጠራል፤ መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡-

- የማርቆስ ወንጌል 12:17 ‹‹ኢየሱስም መልሶ፦ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው። በእርሱም ተደነቁ።››
- ትንቢተ ሚልክያስ 3;8‹‹ ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም። የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በአሥራትና በበኵራት ነው።እናንተ፥ ይህ ሕዝብ ሁሉ፥ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፥ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፦››
- ትንቢተ ሐጌ 1;6 ‹‹ ብዙ ዘራችሁ፥ ጥቂትም አገባችሁ በላችሁ፥ ነገር ግን አልጠገባችሁም ጠጣችሁ፥ ነገር ግን አልረካችሁም ለበሳችሁ፥ ነገር ግን አልሞቃችሁም ደመወዙን የተቀበለ ሰው በቀዳዳ ከረጢት ያደርገው ዘንድ ደመወዙን ተቀበለ።››

7. **ምርጫዉን/አቋሙን የለየ**

AåEr ˆ·Y †E„ nEø ŠAåEr ›Ù L'å»r ˆ¿ªM¨uG AåEå I†EN †¿- '»r \éºY መንፈሳዊ NYÁ'å¿ L'\¿ አለበት። አለማዊና መንፈሳዊ ሆኖ መጓዝ አይቻልም፤ለይጣንን ወይም እግዚአብሔረርን መምረጥ እንጅ መካከለኛ የሚባል ህይወት የለም። ቅዱሳት መጻህፍትም እንዲህ ይመክሩናል፡-

- ❖ መዝሙረ ዳዊት 72(73)፡28 ‹‹ ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል መታመኛዬም እግዚአብሔር ነው ... ››

- **የማቴዎስ ወንጌል 6:24‹‹ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።››**
- ¦˜ 1:8 ; AåEr A]n FE’å lL¿µ- AåEå EM¦’F’åG Ešé¦ \’å ŠµîQ š¿- †¿«v £Më¦µ˜ †¨N\E’å::∪
- **መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 24፡15‹‹ እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።››**

ስለዚህ ŒnY¿ EM·„r l†EN ^¿ኖY †EN Š^{a}µ\vG¿ -·^ **ይልቅ** LG‹Lå¿ £µîq L¿µ- LN¿¼ }’å:: NYÁ ŠEîE¿ ·¿ µå**ዞ**†v¿ ’^{a}ኋF ˆ-µqv¿ ˆ¿^{a} -låbr †TLåu £pOFlr ¨D¿~ Š·mv¿ †¿^{a}Y^N:: ^EšC NYÁ¿ L’\¿ rGi }µY }’å::

8. **ŠዓEN የተለየ፤**

ŠዓEN LE£r \émG nšå•uv¿ ˆW^¿ L»G~ E·G C¨’r ^{a}¿q lé^ LD¿ E^W ErNCYr ˆNn›N አEL¾}i Mሕl**W**”í }åZ¿ Lp’å ¨L^G~G:: }µY ·¿ ŠዓEN LE£r MEr Ô**ቃደ** ^¶¿ Lp’å MEr }’å።

- **ወደ ገላትያ ሰዎች 5□19 ∩የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፤ ርኵሰት፤ መዳራት፤ ጣዖትን ማምለክ፤ ምዋርት፤ ጥል፤ ክርክር፤ ቅንዓት፤ ቁጣ፤ አድመኛነት፤ መለያየት፤ መናፍቅነት፤ ምቀኝነት፤ መግደል፤ ስካር፤ ዘፋኝነት፤ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።∪ ከዓለም መለየት ከነዚህ የሰጋ ሥራዎች መለየት ነዉ።**
- **ወደ ገላትያ ሰዎች 5፤24 “የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።”**
- **የማቴዎስ ወንጌል 16;26‹‹ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?››**

9. l¼ln የሚኖር

W\å¿ l¼l*n* MµGµG ŠEîEøv ¶Y lwFN lLኖY l¼ln LLFE^ **ይኖርበታል፤ ይህንን ጥበብም የምናገኘዉ ከእግዚአብሔር መሆኑን አምነን ማስተዋልን እንዲሰጠን መለመን ያስፈልጋል።**

- **መጽሐፈ ምሳሌ 1□7 ∩የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ።∪**

- መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 1□10 ∩አሁንም በዚህ ሕዝብ ፊት እወጣና እገባ ዘንድ ጥበብንና እውቀትን ስጠኝ፤ ይህን በሚያህል በዚህ በታላቅ ሕዝብ ላይ ይፈርድ ዘንድ የሚችል የለምና። እግዚአብሔርም ሰሎሞንን ይህ በልብህ ነበረና፥ ባለጠግነትንና ሀብትን ክብርንና የጠላቶችህን ነፍስ ረጅምም ዕድሜን አልለመንህምና፥ ነገር ግን ባነገሥሁህ በሕዝቤ ላይ ለመፍረድ ትችል ዘንድ ጥበብንና እውቀትን ለራስህ ለምነሃልና ጥበብንና እውቀትን ሰጥቼሃለሁ።∪
- መጽሐፈ ኢዮብ 28□28 ∩... እነሆ፥ እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው፤ ከኃጢአትም መራቅ ማስተዋል ነው አለው።∪

10. NŒ¿¦r የማይወድ፤

ኃጢአት ለመስራት ሰበብ አስባብ መፍጠርን መተዉ ያስፈልጋል፤ለኃጢአታችን የምናስቀምጠዉ ሰበብ ሁሉ ከበደለኛነት አያስቀረንም፤ይልቁን የሴፍን እንመልከት የንጉሡ ሚስት ለዝሙት ስትጋብዘዉ እኔ እንግዲህ ምን ላድርግ ወጣት ነኝ፤ደግሞ የንጉሥ ሚስት ናት፤ እርሱዋ ስትጠይቀኝ እንዴት እምቢ እላለሁ የሚል ምክንያትና ይሉኝታ አላቀረበም ነበር። ይልቁንም እንዲህ ሲል ነበር የመለሰላት፥-

- ‹‹... እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?›› ኦሪት ዘፍጥረት 39፡9

11. በአቋሙ የጸና፤

ሲመች መንፈሳዊ ሳይመች ዓለማዊ መሆን አይገባም ፤ŠmCY F¨ ˆ¿ª²d ŠålrAåEåN l}«’å]¨µ× lµîq pdm¨}r ¦µ„ š¿- ˆ’å}pƒ †ቁዋN¿ lL¦œ ˆ¿ª ѡE^pý ªfi lˆ]r lé»GN l†ቁዋLå lLÎ~r †NFŠå¿ M]’i †Elr፤ መከራ ሲመጣ የምንሸሸ መሆን የለብንም። «¿.3□29 ˆ}šéC JÑ~r l†kMt’å በLÎ~r ናlåŠª}ÓY¿ £ˆ}\å¿ †NFŒ ˆ¿«é¦N¿ አድርገዉታል።

- ትንቢተ ዳንኤል 3፡17 ‹‹የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል ከእጅህም ያድነናል፥ ... ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቀም'ከውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት።››

12. LG‹N N]Eî የሚሆን፤

l†‹Bñ- lአTML- l†ºgF¨ lL¿Ô]”í C¨¨pý lዓለም \éኖY lRW lL^V¦ lîr lንTlîr †Y¦ LD¿ †Elr ˆ¿«é¦’å ·¿ ŠAåEå ¶Y ˆ¿ª’åa £Më~Š^ ŠD} Œ× †Y†¦ ¨D~G~

- የማቴዎስ ወንጌል 5፡16 ‹‹መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።››

13. RW¿ የሚወድ፤

መንፈሳዊ ሰዉ በሁሉም ራሱን የቻለ ጠንካራ እንጅ ሰነፍ አይደለም፤ሰዉ L¿Ô]"í}r¿ \é¯NY ስራን ˆY·Ù †-Y¸ Lp'å ያለበት የሚመስላቸዉ አሉ፤ ይህ ስህተት ነዉ፤ለምሳሌ በገዳማት ያለዉን የስራ ባህል ስንመለከት ዓለም ራሱ ሊማርበት ይገባ ነበር፤ ˆ¿ª} iዱ^ ጳውሎስ ድንኳን ˆ£\× I^W በL°L- ŠpT³}r LWi }'å ሐዋ.18፡3፤

- 2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 3፡**10** ‹‹ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን፡፡ ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና፡፡››
- ወደ ሮሜ ሰዎች 12፡**11** ‹‹ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ›› የተባለዉን ሁልጊዜ ማስታወስ ይገባናል፡፡

14. I†iN የሚረፍ

ሰዎች በኃጢያት የሰበሰቡትን ገንዘብ በመመልከት ወደ ክፉ ሥራ ከመግባት ይልቅ ባለህ ንጹህ ገንዘብ አመስግኖ መኖር ያስፈልጋል፤

- 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡**6** ‹‹ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፥››

15. "› Ô››¿ †EMn›r

ˆ¿«é¦'å œN nEø lD}'å mGD}'åN "šƒ]¨D}å I^Y—r~ leN }µY LºY ¨µmG:: ¨C \éባG ·¿ ˆ¿«é¦'å ŠMClT\lå ˆ¿Wi MEr †¨ªEN }µY ·¿ £lîpŒY^pí¦¿¿ ˆ~ £ዓEN¿ Aå}ðq LE£r }'å:: lዓEN µnp¿ llîpŒY^pí¦¿ F¨ †ELdE- **አለዚያ ግን** ŠlTŠr ¨Gi LYµN¿ ˆ~pር×E¿::

- *መዝ.1□1 ∩ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ □ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፡፡∪*
- **ኤፌሶን 5፥4∩የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ፥ ይልቁን ምስጋና እንጂ፡፡∪**

16. LŠmlY

ˆµEî }Ã Emb }'å□ ˆµEî ªB }'å□]¨Eå ŠAåEN ¶Y lˆŠåG lLŠmlY lLp]\nና በመደማመጥ ˆ}ð nu ¨-F„ £M¨G LD¿ †Elr:: l†ºgF¨ L¿Ô]"í '»ሎv I—EN \éኖU ElF©ut'å £ሚታዘዙ El¸ ^W AåEå £"C~ i¿}ት¿ £Më¦]¤ LD¿ †Emtው፡፡

- ∩ˆY^ lር]vAå ÙiY léኖWvAå ደd L›LåYpò ˆ¿ªD~vAå \•v AåEå lšéC ¦'ågEå፡፡∪ ©H 13□35 ˆ¿«E
  - ∩የጌጥ ልብስም የለበሰውን ተመልክታችሁ፡፡ አንተስ በዚህ በመልካም ስፍራ ተቀመጥ ብትሉት□ ድህውንም አንተስ ወደዚያ ቁም ወይም ከእግሬ መረገጫ በታች ተቀመጥ ብትሉት□ ራሳችሁን መለያየታችሁ አይደለምን?›› የያዕቆብ መልእክት 2□3

17. lEîEøv †ELÙT-:-

lEîEøv ŠLÙT- lL¯LV¦ lW^ ላ¨ LÙT- Š†¨¿C ያE'å¿ N_]q'» ^EN¿ lEîEøv ¦E'å¿ µå-Ù q¦EC ˆ¿«¨ÔT-mvAå †rÙTዱ l\ÔWvAår L^ÔV¦ ¨\ÔYmvyG~

- ∩ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፤ እርሱም ሊያድን ሊያጠፋም የሚችል ነው፤ በሌላው ግን የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?›› የያዕቆብ መልእክት 4□12
- ∩አንተም እንደዚህ በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንም የምታደርግ ሰው ሆይ□ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን?››ወደ ሮሜ ሰዎች 2□3

18. £lîpŒY^pí¦¿¿ ^Y—r L°li

የቤተክርስቲያንን ስርዐት አዉቀና ተምሮ ምን አለበት በሚል የተሳሳተ ፈሊጥ በራስ ሀሳብ አለመመራት□ መጠየቅ አለመቻላችን ቤተክርስቲያን ለእያንዳንዱ ስርዐት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ አላትና፤

- ∩ወንድሞች ሆይ፥ እንመክራችኋለን፤ ያለ ስርዐት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤ ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፤ ለደካሞች ትጉላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ።››1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5□14
- 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 14፤40 " ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።"

19. ¤lîpŒY^pí¦¿ †msv ጸሎር ^ር eÃ nEø LMY

‹GpMU M'i ቃሉን L°li £EN~ lዓEN ^¿ኖY eÃ nEø LMY ¨µmG:: eÃ nEø ¦GpMT Cµå¿ †'åj Cµå¿ L°li Šy°éአr መWi ያልቻለ }µ M^pMY †¨vGN~፤ lšéC ሰራዋ MY¦N ˆCp †Gዓ›Y ∩...LG‹N ˆ-G¿ LT°v።∪ pnFEv Eåg.10:42

20. ወደ ቤተክርስቲን መሄድ

መዝሙረ ዳዊት 122፤1‹‹ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ።››

በዚህ ጥቅስ መሰረት ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ የሚያስደስት ከሆነ ሁልጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ልንገሰግስ ይገባል ምክንያቱም ይህንን በማድረጋችን በርካታ ጥቅሞችን እናገኛለንና ለአብነት ያህልም፡-

- **የምንሰራዉ ሐጢያት ስለሚስጨንቀንና ለዚህ መድሐኒቱ ደግሞ እግዚአብሔር ስለሆነ የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት ስንል ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን፤**
- **የመንፈስ ጭንቀት ሲደርስብንና ሰላም ስናጣ የሰላም አለቃ ጌታችን ክርስቶስ ሰላም እንዲሰጠን ለመጠየቅ፤ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን፤**
- **በርካታ በአይን የማናያቸዉና በእጅ የማንዳስሳቸዉ የእግዚአብሔር ጸጋዎችን ለመሳተፍ፤ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን፤**
- **ሁለት ወይም ሶስት ሆነዉ በስሜ ቢሰባሰቡ እኔ በመካከላችሁ እገኛለሁ ያለዉ ባለዉ ቃል መሰረት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ለማድረግ፤ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን፤**

- በእግዚአብሔር ቤት ዉስጥ ሆኖ የሚቀርብ ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ ይበልጥ ተቀባይነት ስላለዉ ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን፤
    - መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 8:29 ‹‹ባሪያህ ወደዚህ ስፍራ የሚጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ። በዚያ ስሜ ይሆናል ወዳልኸው ስፍራ ወደዚህ ቤት ዓይኖችህ ሌሊትና ቀን የተገለጡ ይሁኑ።››

3.5 የቅድስና ደረጃዎች፤

እንግዲህ ከላይ የተመለከትናቸዉን ነጥቦች አንድ ወጣት ክርስቲያን ደረጃ በደረጃ የሚያሙዋላቸዉ እና የሚደርስባቸዉ አንጅ በአንድ ሌሊት ከሁሉም እደርሳለሁ ቢሉ ዉድቀት ይመጣል፤ ስለዚህ ክርስትና ቀስ በቀስ የሚወጡት ደረጃ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል፤ቤተክርስቲያናችን የቅድስናን ማዕረጋትን በአሰር ከፍላ ታስተምራለች፤

1. ንጽሐ ሥጋ

    1.1 ጽማዌ

    ማለት ዝም ጸጥ ማለት፤ መለፍለፍ መቀባጠርን መተዉ ፤ማቆም ማለት ነዉ፤ሕሌናቸዉ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማሰብ ይችል ዘንድ የዚህን አለም ዉጣ ዉረድ ከማሰብ ከማሰብና ከማዉራት ይከለክሉታል፤

    - የያዕቆብ መልእክት 3፤6 ‹‹አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃጠላል።››

    1.2 ልባዌ

    ማለት ልብ ማድረግ ማስተዋል ማለት ነዉ፤ከዚህ ማእረግ የደረሱ መላእክትን ሲወጡ ሲወርዱና ሲላላኩ ከማየት ባሻገር ለምን እንደሚወጡና እንደሚወርዱም ያዉቃሉ፤

    1.3 ዝማሬ

    ጣዕመ ዝማሬ ማለት ቅዱሳን መላዕክት የሚጸልዩትን ጸሎትና የሚያመሰግኑትን ምስጋና አንድ በአንድ ምሥጢሩንና ትርጉሙን ማወቅ እንዲሁም ያንኑ ምሥጋና ሲያመሰግኑ አለመሰልቸት ነው። ከዚህ መዓርግ የደረሱ ቅዱሳን የሚጸልዩትን ጸሎትና የሚያመሰግኑትን ምስጋና ሲጸልዩት ቢውሉና ቢያድሩ አይሰለቻቸውም። ምክንያቱም ምሥጢሩ እየገባቸው በማስተዋል ስለሚያደርጉት ነው። ‹‹ **እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና በማስተዋል ዘምሩ**›› እንዲል ። መዝ. 46/47÷7 ።

2. **ንጽሐ ነፍስ**

    ንጽሐ ሥጋ ከትሩፋት ሥጋ እንደሚገኝ ንጽሐ ነፍስ ደግሞ ከትሩፋት ነፍስ ይገኛል። ከትሩፋት ነፍስ ትሩፋት ሥጋ እንደሚቀድም እንዲሁም ከንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ሥጋ ይቀድማል። በንጽሐ ነፍስ የሚገኙት አራቱ መዓርጋት የሚከተሉት ናቸው።

    1.1 አንብዕ

እንባዕ ማለት ፊታቸው ሳይከፋውና ሳይሰቀቁ እንባ ከዓይናቸው እንደ ሰን ውኃ ማፍሰስ ነው። ይኸውም ጌታችን ‹‹ ዛሬ የሚያዝኑና የሚያለቅሱ ብፁዓን ናቸው።›› ማቴ.5፤4 .ክቡር ዳዊት ‹‹በእንባዬ መኝታዬን እርሳለሁ›› እንዳለ ከአንዳንድ ቅዱሳን ከዓይናቸው የሚፈሰሰው እንባ ሰሌን እስከ ማራስ ይደርስ እንደ ነበር ዜና ሕይወታቸው ይናገራል። መዝ. 6÷6 ለምሳሌ ቅዱስ አርሳንዩስ ሁል ጊዜ ከማልቀሱ የተነሣ ዕንባው የሚወርድበት በደረቱ ላይ የጎደጎደ ልዩ ሰንበር አውጥቶ ነበር።

1.2 ኩነኔ

በመዓርጋት ሂደት ቅዱሳን በሲኦልና በገነት ያሉ ነፍሳትን ማየት ይችላሉ። ቅዱሳን ከኩነኔ መዓርግ ላይ ሲደርሱ ፈቃደ ሥጋቸው ፈጽሞ ለነፍሳቸው ይገዛል። ሥጋ የነፍስ መሣሪያ ይሆናል። ነፍስ ሥጋን የወደደችውን ታሠራዋለች። መሰገድ ÷ መጾም ÷ መጸለይ ሁሉም ቀላልና ጠባይአዊ እስኪሆኑ ይደርሳሉ።

1.3 ፍቅር

ፍቅር ማለት እግዚአብሔር ከመፍጠር ያልናቀውን ፍጥረት ሁሉንም አስተካክሎ መውደድ ማለት ነው። ኃጥአንና ጻድቅ አማኝና መናፍቅ እንዲሁም ወዳጅና ጠላት ብሎ መለያየት ሳይኖር ማንኛውንም ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል በክብር የተፈጠረ ሰለ ሆነ ብቻ መውደድ ነው። ‹‹**የሚወዷችሁን ብቻ ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?**›› ተብሏልና። ማቴ 5÷47።

1.4 ሐሰት

ሐሰት" ማለት ካሉበት ቦታ ሆኖ ካሰቡት መድረስ ነው። ይኸውም ካንድ ቦታ ሆነው ሌላ ቦታ የሚሠራውን ያውቃሉ። ለምሳሌ ነቢዩ ኤልሳዕ በኢየሩሳሌም ሆኖ የሶርያው ንጉሥ ወልደ አዴር እልፍኙን ዘግቶ ከባለ ሟሎቹ ጋር የመከረውን ምክር ማንም ሰው ሳይነግረው ያውቅበት ነበር። 2ኛ ነገ 6÷8-12 ፣ 31-33። ሐዋ.5፤1-4

3. ንጽሐ ልቦና

ከንጽሐ ነፍስ ማዕረግ የደረሱትን ሊያመጡትና ወደ ፍጹምነት ደረጃ ሊደርሱበት ስለሆነ ጠላት ዲያቢሎስ ያለ የሌለ ኃይሉን ይዞ ይዋጋቸዋል። ሕሊናቸውን በማባከንና በማስጨነቅ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ይለያቸዋል ብሎ የሚያስበውን ልዩ ልዩ ፈተና ሁሉ ያመጣባቸዋል። በሰው እያደረም ይበጠብጣቸዋል፣ ይጣላቸዋል። ይህን ሁሉ ካለፉና ድል ከነሱት እርሱ ራሱ ወታደር÷ ሽፍታ እየመሰለ እየመጣ ይደበድባቸዋል÷እባብ ዘንዶ እየመሰለ ይጠመቀመባቸዋል÷ እንዲሁም አንበሳና ነብር ሌሎችንም ሰውን የሚያስደነግጡና የሚያስፈሩ አራዊትን እየመሰለ ያስፈራራቸዋል።

3.1 ንጻሬ መላዕክት

በንጻሬ መላእክት መዓርግ በዓፀደ ሥጋ ሆነው መላእክትን በየከተማቸውና በየቦታቸው ያያሉ። በሶስቱ ዓለመ መላእክት በኢየር በራማና በኤረር ያሉ ቅዱሳን መላክትን በየነገዳቸውና በየአለቃቸው እንዲሁም በየክፍለ ቦታቸው ሆነው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ ያያሉ። 2ኛ.ቆሮ.12፤2

3.2 ተሰጥሞ ብርሐን

ተሰጥሞ ብርሃን ማለት በብርሃን ባሕር ሲዋኙ ማደር ነው። ይህም ብርሃን ሲያዩት ዓይን የማይበዘብዝና ሰውነትን የማያቃጥል ነው። የብርሃኑም መዓዛና ጣዕም እጅግ አስደሳች ነው።በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ቅዱሳን ሥላሴን ያያሉ፤

3.3 ከዊነ እሳት

ከዊነ እሳት የመጨረሻው መዓርግ ሲሆን እዚህ ደረጃ የደረሱ ቅዱሳን ሰውነታቸው ለኢጋንንት የሚያቃጥልና የማይቀረብ ይሆናል። ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ከዚህ መዓርግ በመድረሱ ተሐዋስያን ከሰውነቱ ሲያርፉ እሳት እንደገባ ጅማት እየተኮማተሩና እያረሩ ሲወድቁ ቅዱስ ኤፍሬም ተመልክቷል። ከዚህ መዓርግ የደረሱ ቅዱሳን ለነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ ይበቃሉ÷ ሥላሴን ያያሉ ÷ የጌትነቱ ብርሃን በሕሊናቸው ይገለጽላቸዋል። ‹‹ብፁዓን ንጹሐነ ልብ እስመ እሙንቱ ይሬእይዎ ለእግዚአብሔር ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው ÷ እግዚአብሔርን ያዩታልና›› ማቴ.5፤8 እግዚአብሔርን ከማየት የበለጠ ፀጋ ስለ ሌለ ከዚህ በኋላ ሌላ ጸጋና ክብር አይሹም።

4. የእግዚአብሔር ህልውና

4.1. ትርጉም

እግዚአብሔር ተብሎ ወደ ግዕዝ የተተረጎመው በዕብራይስጡ ቋንቋ ኤል ወይም በብዙ ቁጥር ኤሎሂም የሚለው ቃል ነው። ኤል ማለት ኃይል ማለት ነው። ኤልሻዳይ ሲል ደግሞ ሁሉን ቻይ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌሎችም የእግዚአብሔር ስሞች ይገኛሉ። ለምሣሌ ያህዌ ማለት የነበረ□ ያለና የሚኖር ማለት ነው። አዶናይ ማለት ደግሞ ጌታ ማለት ነው።

እግዚአብሔር የሚለው የግዕዝ ቃል ወደ አማርኛ ሲተረጎም እግዚ ማለት ጌታ፤ ብሔር ማለት ዓለም ሲሆን የሀገር/ የዓለማት ጌታ ማለት ነው።ህልውና ማለት ደግሞ መኖር ማለት ነው።

4.2. የእግዚአብሔር ህልውና

ቀና ብለን ወደላይ ብናይ፥ጐንበስ ብለን ወደመሬት ብንመለከት፥ወደ ቀኝና ወደ ግራ ዞር ዞር ብንል ዘለዓለማዊ□ የሁሉም ገዢ□ ዐዋቂ□ ብልኅ□ በሁሉም ቦታ የሚገኝ□ ቦታ የማይወሰነው አንድ ፈጣሪ ለመኖሩ ግልጽ የሆኑ ምልክቶችንና ማስረጃዎችን እናገኛለን። ሰማይና ምድር እንዲሁም የእግዚአብሔር ክንዋኔዎች ሁሉ በአንድ ድምፅ ሆነው የፈጠራቸውና ሥነ ሥርዓትን ያስያዛቸው አንድ አምላክ መኖሩን በመግለጽ ይመሰክራሉ።

ቃለ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ‹‹ወፎችን ና እንስሳትን ብትጠይቁአቸው ብዙ ሊያስተምሩአችሁ በቻሉ ነበር። በምድር ላይና በባሕር ውስጥ የሚኖሩትን ፍጥረታት ጥበብ እንዲያስተምሩአችሁ ብትጠይቁአቸው ሁሉም እግዚአብሔር እንደሠራቸው ያስረዱአችኃል። የፍጥረቶቹን ሕይወት የሚመራ እግዚአብሔር ነው፣የእያንዳንዱ ሰው ነፍስ በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ነው።›› /ኢዮ 12.7-10/

በተለየ ለእግዚአብሔር ህላዌ ማስረጃነት የሚቀርቡ፦

1/ የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓትና አመራሩ፣

2/ የጎሊና ምስክርነት፥

3/ የሰው ልጆች የተፈጥሮ ዝንባሌ፥

4/ የቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ምስክርነት

1. የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓትሩ

የክረምትና የበጋው የቀንና የሌሊቱ የብርሃንና የጨለማው የሙቀትና የብርዱ የዝናብና የብራው፥የልምላሜና የድርቁ፥የዘርና የመከሩ ጊዜያት መፈራረቅ እንዴት ጊዜአቸውን ጠብቀውና ሥነ ሥርዓትን ተከትለው የሚካሄዱ መሆናቸው የሚያመለክተው እነዚህ ሁናቴዎች ያለ አንድ የበላይ ጠባቂ እና ተቀጣጣሪ ሊካሄዱ የማይችሉ መሆናቸውን ነው። እንዲሁም የሰው ልጅ አፈጣጠር አወላለዱ አስተዳደጉ የሰውነት ክፍሎቹ ሥነ ሥርዓት፥ማለት በእግሩ ለመራመድና ለመሄድ፥በእጅ ለመዳሰስ ለመያዝና ለመሥራት በዐይኑ ለማየት በጆሮው ለመስማት በአንደበቱ ለመናገርና በምላሱ ለመቅመስ በአፋና በጥርሱ ለመብላትና ለመጠጣት በአፍንጫው ለማሽተት እንዲችል ሆኖ መፈጠሩ አለሙ የተፈጠረበትን ሥነ ሥርዓት ያሳየናል።

የአፈጣጠሩ ድንቅነትና የማይዛባ የተፈጥሮ ሥነ ሥርዓት የሚያመለክቱት የእግዚአብሔርን ክብር ለመሆኑ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 18/19 ቁ 1 ላይ ‹‹ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣የሰማይ ጠፈሮችም የእግዚአብሔርን ሥራ ያውጃሉ›› በማለት አድናቆቱን ገልጾአል። እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ምዕ.1 ቁ.20 ላይ ፡-‹‹ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለሰዎች የሚታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይኸው ዘለዓለማዊ ኃይሉና አምላክነቱ እርሱ በፈጠራቸው ነገሮች ግልጽ ሆኖ ታይቶአል።›› በማለት ፍጥረቶች እንዴት ስለ እግዚአብሔር ህላዌ ማስረጃ እንደሆኑ ይገለጻል።

2. ***የጎሊና ምሰክርነት-***

ማረጋገጫ የሰጠው፥-የሙሴ ሕግ የሌላቸው አረማውያን በተፈጥሮአቸው ሕግ የሚያዝዘውን ነገር ይፈጽማሉ። በዚህም ምክንያት የሙሴ ሕግ ባይኖራቸውም የራሳቸው የተፈጥሮ ሕግ ስላላቸው ማድረግ የሚገባቸውን ያውቃሉ። ይህም ሁኔታቸው የሙሴ ሕግ የሚአዝዘው ነገር ሁሉ በልባቸው የተጻፈ መሆኑ ያሳያል። ደግሞም ጎሊናቸው ይመሰክርባቸዋል። ጎሊናቸው አንዳንዴ ይወቅሳቸዋል፣እንዳንዴም ይደግፋቸዋል።

3. **የሰው ልጆች የተፈጥሮ ዝንባሌ፥-**

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኝ ሰው ሁሉ እርዳታውና ጥበቃው የሚፈለግ፥ፍጹምነትን የተመላ፥ደግ፥ሁሉን ቻይ፥ሰውን የሚወድ፥ሊወደድና ሊሰገድለት የሚገባ አንድ አምላክ ያለመሆኑን በማመን ይስማማሉ።ዓለምን የዞሩ ሰዎች እንደመሰከሩት ይህ በሰው ልጆች ዘንድ ያለው የእምነት ዝንባሌና ስሜት ለሕይወት አስፈላጊ ከሆኑ ከሌሎቹ የተፈጥሮ ፍላጎቶች ምንም ልዩነት የሌለው ሆኖ አግኝተውታል።

ይህም ማለት የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መኖር የሚያምነው በጽሑፍ የቀረበለትን የሃይማኖት መጽሐፍ በማንበብ ወይም የሃይማኖት አስተማሪ ስለሚሰብክለት ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ስሜቱ፣ፍላጎቱ፣ወይም ዝንባሌው ስለሚገፋፋውም ጭምር ነው።ይህንኑ የሰውን ሃይማኖታዊ ዝንባሌ በመጠቀም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በአቴና ከተማ ውስጥ በሚገኝ በአንድ የአምልኮ ቦታ ለማይታወቅ አምላክ ተብሎ ተጽፎ ያገኘውን ጽሑፍ መነሻ በማድረግ አርዮስፋጎስ በተባለው ስፍራ የክርስትናን ሃይማኖት ለመስበክና አንዳንድ ሰዎችን ለማሳመን የበቃው /የሐ.ሥ.ም.17.ቁ.22-34/

4. የቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ምስክርነት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ልዩ ትንቢቶች ተነግረው እነዚያም የተነገሩት ትንቢቶች በየጊዜያቸው የተፈጸሙ መሆናቸው በታሪክም ጭምር የተረጋገጠ ነው። ወደፊት የሚደርሰውን ሁናቴ አስቀድመው እንዲናገሩ በልዩ ልዩ መንገድ ለነቢያት የገለጸላቸው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም የነበረ□ ያለና የሚኖር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ህልውና ካረጋገጠባቸው ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

- መዝሙረ ዳዊት 10□4 ∩ኃጢአተኛ እግዚአብሔርን አበሳጨው□ እንደ ቍጣውም ብዛት አይመራመረውም□ በእርሱ ፊት እግዚአብሔር የለም።∪

4.2. የእግዚአብሔርን ህላዌ የሚያመለክቱ ባህርዮች፤

ባህርይ ማለት የአንድን ነገር ምንነት የሚገልጽ ቃል ነው። የእግዚአብሔር ባህርይ ሲባል ደግሞ በእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ የሚገለጡትን ሁኔታዎች የሚያመለክት ነው። የእግዚአብሔር ፍጥረቶችን ጠባዮች ለመግለጥ እንደሚቻለው የእግዚአብሔርን ባህርይ በእኛ ውሱን አስተሳሰብ በትክክል ለመግለጥ አይቻለንም። በተለያዩ አርእስት ሥር ከፋፍሎ ለማስረዳት የተሞከረው ግን እኛ ውሱኖቹ በሚገባን ቋንቋና ለአስተሳሰባችን በሚያመች መንገድ ለማቅረብ ታስቦ ብቻ ነው።

በዚህ ርእስ ሥር የሚጠቃለሉት የእግዚአብሔር ባህርዮች ሰብአዊ ፍጡር ሊናገው የማይችል የእግዚአብሔር የባሕርዩ ገንዘቦች ብቻ ናቸው። እነርሱም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል።

1. ***እግዚአብሔር በራሱ መኖር***- የእግዚአብሔር በራሱ መኖር በምንም ነገር ውሱን ካለመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ጠባይ ለእግዚአብሔር እንጅ ለማንኛውም ፍጡር የሚነገር አይደለም። እግዚአብሔር በራሱ የሚኖር ሲሆን ፍጥረቶቹ ግን በእግዚአብሔር አማካኝነት ካልሆነ በቀር በራሳቸው ሊኖሩ አይችሉም።∩ እግዚአብሔር የነበረ□ ያለና ወደፊት የሚኖር ነው።∪ ዮሐ.5□26።ዘጸ.3፤14።ራዕ.22፤13።
2. ***የማንም እርዳታ የማያስፈልገው መሆኑ*** ሰዎች በአስተሳሰባቸው ስለእግዚአብሔር የሚያውቁት እርሱ የማንም እርዳታ የማያስፈልገው መሆኑን ነው።ቅዱሳት መጻሕፍትም በሚቀጥሉት ጥቅሶች ይህን አባባል ያረጋግጣሉ።
   - ∩የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚያዉቅ ማንም የለም□ የእርሱ አማካሪ የሚሆንም የለም∪ ሮሜ11□34
3. ***የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት*** ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው እግዚአብሔር የማንም እርዳታ የማያስፈልገው በራሱ የሚኖር ህልው ነው። ህላዌውን በሚገልጡት ጠባዮቹ እርሱ ከዘመናት በላይ ሆኖ እርሱ የፈጠራቸው

ፍጥረቶች ግን በእርሱ አንቀሳቃሽነት በዘመናት ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ። እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ነው።እርሱ ከሰብአዊ ፍጡር ከሚለይባቸው ምክንያቶች አንዱ ምክንያት በዘመን ውስጥ መጀመሪያ የሌለውና እንደ ሰው መጨረሻ ኖሮት ሌላ ሕይወት የሚጀመር አለመሆኑ።

- ‹‹ተራሮች ሳይወለዱ ምድርም አለምም ሳይሰሩ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አንተ አምላክ ነህ›› ።መዝ.89/90 2

4. ***የእግዚአብሔር አለመለወጡ*** መለወጥ ማለት ቀድሞ ያልነበሩትን ሁናቴ መሆን ወይም ካሉበት ሁናቴ ወደ ሌላ ሁናቴ መዛወር ማለት ነው። ሳይለወጡ ባለው ሁናቴ ጸንቶ መኖር ከዘለዓለማዊነት ጠባይ ጋር የተያያዘ ነው።
   - ∩እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም∪ ሚል.3 6
5. ***እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሚገኝ መሆን/ወሰንነት የሌለበት መሆኑ*** በሁሉም ቦታ የመገኘቱ ትምህርት በሁለንተናው በሁሉም ቦታ መገኘቱ የሚለውን ሥነ መለኮታዊ ትምህርት ያስከትላል። እግዚአብሔር በጊዜ እንደማይወሰን ሁሉ በቦታም አይወሰንም። ስለዚህ እግዚአብሔር በጊዜ ወይም በዘመን ያልተወሰነ ዘለዓለማዊ የማይለወጥ በሁሉም ቦታ የሚገኝና በምንም ነገር ያልተወሰነ መንፈስ ነው። የእግዚአብሔር ውሱን አለመሆን ዋናው ምልክት በሁሉም ቦታ መገኘቱ ነው። ይህም ደግሞ የእግዚአብሔርን ህላዌ ያመለክታል። የእግዚአብሔር በሁሉም ቦታ መገኘት ጠባይ ደግሞ የእግዚአብሔር ውሱን አለመሆን ነው።
   - ∩ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ እስከ ባህር መጨረሻም ብበር በዚያ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ትይዘኛለች∪ መዝ.138/139 7
   - ∩ *ሰማይና ምድርን የሞላሁ እኔ አይደለሁምን∪ ኤር.23* 24
   - ∩የእግዚአብሔርን የዘመኑንም ልክ ሊቆጥር የሚችል የለም።∪ ኢዮ 36 26

4.3. ከፍጥረቱ ጋር ባለው ግንኙነት የእግዚአብሔር ጠባዮች፣

የእግዚአብሔር ግርማና ልዕልና በሥራዎቹ ይገለጣል። የእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉ ጠባዮች ሁሉን ነገር ዐዋቂነቱና ፍጹም ጥበበኛነቱ ናቸው። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚጠቃለሉት ጠባዮች ደግሞ ሁሉን ቻይ ቅዱስነት ጽድቅ ደግነት ወይም ፍቅር እውነተኛነት ናቸው።

1. ***የእግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂነት*** እግዚአብሔር ***ሁሉን*** ያውቃል፣ ራሱን ያውቃል፣ ከእርሱ የሚወጣውንም ያውቃል። ፍጹም መንፈስነትና ውሱን ያለሆነ ባሕርይ ስላለው እርሱ ራሱን የሚያውቅ ለመሆኑ በእርግጠኛነት ልንገምተው እንችላለን። ፍጹም መንፈስነት ያለው እንደመሆኑ እንዴት ራሱን አያውቅም? ያውቃል እንጂ በዚህም ራሱን በማወቅ ረገድ ሕጸጽ ሊኖረው አይችልም። ራሱን በማወቅ ውሱንነት ከሌለበት በሐሳቡም ውሱንነት አይኖረውም፣ በእርግጥም ውሱንነት የለውም።
   - ‹‹*ሰዉ በሰዉር ቢሸሸግ እኔ አላየዉምን ሰማይና ምድርን የሞላሁ እኔ አይደለሁምን›› ኤር.23 24*

2. ***የእግዚአብሔር ጥበበኝነት*** የእግዚአብሔር ጥበበኝነት ሁሉን ነገር ከማወቁ ጋር የተያያዘ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ጥበበኝነት ጠባይ የአግዚአብሔርን ከፍተኛ ዓላማዎች የሚያመቻች ነው። በዚህም ጠባይ አማካይነት ዓላማዎቹን ተግባራዊ የሚያደርግባቸውን የተሻሉ ዘዴዎችን ይመርጣል። በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር ጥበበኝነት ራሱ እንደ እግዚአብሔር ዕውቀት መታየት ይችላል። እርሱም የእግዚአብሔር ዕውቀት ተግባራዊ ነው ሊባል ይቻላል።

   ❖ ∩እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣል ከአፉም እዉቀትና ማስተዋል ይወጣሉ∪ ምሳ.2□6

3. ***የእግዚአብሔር ቅዱስነት*** ቅዱስ የሚለው ቃል ትርጉም ከተራ ነገር ወይም ከርኩሰት ልዩ መሆን ማለት ነው፣ እግዚአብሔር ከርኩሰትና ከሕጸጽ ነፃ መሆኑን የሚያመለክተው ጠባይ ቅዱስነት ይባላል። በዕብራይስጥና በግሪክ ቅዱስነት ከመለኮት ጋር የተያያዘ ነው።

   ❖ ∩እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ∪ ዘሌ.19 □2

4. ***የእግዚአብሔር ጽድቅ /ፍትሕ/-*** ከእግዚአብሔር ቅድስና ጋር የእግዚአብሔር ጽድቅ መገኘቱ ግልጥ ነው። ፍትሕ ማለት ትክክለኛ ፍርድ ማለት ሲሆን ጽድቅ ማለት ደግሞ እውነተኛነት□ ከሐሰትና ከኃጢአት መለየት ነው። እነዚህ ሁለት ቃላት በእግዚአብሔር ጠባይነታቸው በሚነገሩበት ጊዜ ተወራራሽነት አላቸው። በዚህም ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ጽድቅና ፍትሕ የሚቀርቡት በአንድነት ነው።

   ❖ ∩እግዚአብሔር የእዉነት ዳኛ ነዉ∪ መዝ.7□11

5. ***የእግዚአብሔር ፍቅርና ደግነቱ*** ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ደግነት በምንነጋገርበት ጊዜ የእርሱ ደግነት ከሌላ ሁሉ የተለየ መሆኑን መገንዘብ አለብን። እግዚአብሔርም የደግነት ሁሉ ምንጭ ሲሆን የደግነቱም ዐይነት ፍጡር ከሚኖረው ደግነት የተለየ ነው። የሰዎች ደግነት ከእግዚአብሔር ደግነት ጋር ሊነጻጸር አይችልም ደግነት በባሕርዩ ያለ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ደግነትም ከእግዚአብሔር ጠባዮች አንዱ ነው።

   ❖ ‹‹እግዚብሔር ምንኛ ደግ እንደሆነ ቅመሱ እዩም በእርሱ የሚታመን ሰዉ ምስጉን ነዉ።›› መዝ.34□8

6. ***የእግዚአብሔር እውነተኝነትና ታማኝነት*** ወንጌላዊው ዩሐንስ እንዳለው ∩እግዚአብሔር እውነተኛ ነው።∪ /ዮሐ.ም.3 ቁ.33/ ባለመዝሙሩም ∩የእግዚአብሔር መንገዶች ሁሉ ምሕረትና እውነት ናቸው።∪ ብሎአል።/መዝ.25 ቁ.10/

   በዚህም መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር÷ሐሰተኛነት÷ቃልኪዳን አለመጠበቅና ቀጠሮ ማፍረስ እንደሌለበት ይገልጣሉ። ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ፍጹምና ውሱንነት የሌለበት ነው። እግዚአብሔር በኃያልነቱ÷በደግነቱና በዐዋቂነቱ ውሱንነት የለበትም። እነዚህም ጠባዮች እርሱ በንግግሩና በቃል ኪዳኑ ታማኝና እውነተኛ መሆኑን ያመለክቱናል።

- ‹‹ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፣ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም፣ እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን?›› /ዘኁ.ም.23 ቁ.19/

7. ***የእግዚአብሔር መንፈሰነት*** በዚህ የእግዚአብሔርን መንፈሰነት በተመለከተ የሚቀርቡት ማስረጃዎች፤፤
   - **የዮሐንስ ወንጌል 4፤24‹‹ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል››**

5. የክርስትና ትምህርት ምንጭ/መነሻ

5.1. የክርስትና ትምህርት ምንጮች፡-

1. *መጽሐፍ ቅዱስ*
2. ትውፊት፣
3. ዲድስቅልያ
4. ቅዱሳን አባቶችና ሲኖዶሶቻቸው ናቸው።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም በቅደም ተከተላቸዉ በአጭሩ እንመለከታቸዋለን ፡-

5.1.1. መጽሐፍ ቅዱስ

SêNõ TKƒ Ÿc¨< MÐ‹ ›°Ua“ Hdw ’p„ S”ß„ u›°Ua ›³»’ƒ u¨[kƒ' ukKU“ uw°` ¾T>k[ê ¾T>✶Ã w‰ XÃJ” ¾T>’uw ¾çNò¨<” Hdw eT@ƒU J’ ›sU ¾T>ÑMê Y°M /ö„ Ó^õ/ ’¨< TKƒ Ã‰LM:: **መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በቀጥታ ሲተረጎም ቅዱስ መጽሐፍ ማለት ሲሆን የተቀደሰ /የተለየ/ መጽሐፍ ማለት ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ሲያሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል። /2ጢም3፤15/ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገሩ የብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥራዝ ነው ። የመጀመሪያው መጽሐፍ መጽሐፈ ሄኖክ ሲሆን ዛሬ በዓለም ላይ የተለያየ እድሜ፣ መጠን እና ይዘት ያላቸው መጻሕፍት አሉ።**

¾SêNõ pÆe ¯LT

c¨< ¾✡Ó²=›wN?`” GXw °pÉ“ ðnÉ K=Á¨<k¨< ¾T>‹K¨< ŸSêNõ pÆe ’¨<:: cK²=l ¾SêNõ kÆe ª’— ¯KT ¾✡Ó²=›wN?`” ¾õp` Y^ Ndu<” °kÆ” ðnÆ”U Kc¨< Te✶¨p ’¨<::Ã¤¨<U c¨‹ G<K< ›=¾c<e ✡`c< ¡`e„e ¾✡Ó²=›wN?` MÏ ⁕✡”ÅJ’ ✡”Ç=ÁU’<“ ›U”¨<U ueS< QÃ¨ƒ ⁕✡”Ç=J”L†¨< SÓKê ’¨<:: /ÄN 20 30-3ı/ SêNõ pÆe ¾õp` SM°¡ƒ eKJ’ c¨‹ G<K< }óp[¨< ✡Ó²=›wN?`” uS¨<ÅÉ KnK<U uS✶²′ ¾¡w` ƒ”d›?”“ ²LKT© lÃ¨ƒ” u}eó ✡”Ç=Öwl ÃÑMéM: Á’nnM ::

¾SêNõ pÆe ²K¯KT©'ƒ !

SêNõ TKƒ Ÿc¨< MÐ‹ ›°Ua“ Hdw 'p„ S”ß„ u›°Ua ›³»'ƒ u¨[kƒ' ukKU“ uw°` ¾T>k[ê ¾T>✶Ã w‰ XÃJ” ¾T>'uw ¾çNò¨<” Hdw eT@ƒU J' ›sU ¾T>ÑMê Y°M /ö„ Ó^õ/ ”¨< TKƒ Ã‰LM:: ***መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በቀጥታ ሲተረጎም ቅዱስ መጽሐፍ ማለት ሲሆን የተቀደሰ /የተለየ/ መጽሐፍ ማለት ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ሲያሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል። /2ጢም3፤15/ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገሩ የብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥራዝ ነው ። የመጀመሪያው መጽሐፍ መጽሐፈ ሄኖክ ሲሆን ዛሬ በዓለም ላይ የተለያየ እድሜ፣ መጠን እና ይዘት ያላቸው መጻሕፍት አሉ። የ✡Ó²=›wN?` nM ”¨< :: eK²=I K²K¯KU Ã⁕^M ::/T,5'17'25/ u¦ÚT]U ¾SêNõ pÆe ✡eƒ”óe ⁕✡Ó²=›wN?` ”¨<::²Ç 31&9 Q′ 2'7 2— Ö=V3'17 2— â?Øa 1'21/ :: ⁕***

¾SêNõ pÆe çNò-‹

SêNõ pÆe” ¾é÷ƒ pÆd” “†¨< 'Ñ` Ó” Ÿ^X†¨< ›S”ß¦¨< dÃJ” u✡Ó²=›wN?` ¦MŸ¨<“ ***ታ'²***¨< ”¨< SêNõ pÆe” ¾éñ c¨‹ Ÿ¦KÁ¾ ¾e^ Se¡ ¾¦Ö\ “†¨< :: KUdK? ”Ñ<Y' U`¢“ ' ✡[— K=p'¯X ›ØTÏ ' k^ß ' NŸ=U ... 'u\ u¦KÁ¾ ›Ñ`“ u¦KÁ¾ ²S” ¾'u\ cKJ'< ›w³—-‡ ›Ã¦ª¨lU 'u`:: wK<Ã Ÿ=Ç”” Ÿ40 W¨‹ uLÃ ›Ç=e "Ç”” ÅÓV ŸeU”ƒ c¨‹ uLÃ êð¨<***ታ***M :: ›Vî 7'14

T, 9'9 T, 4'21 qL 4'14/

SêNõ pÆe ¾¦éðuƒ ²S” '

wK<Ã Ÿ=Ç” Ÿ1400 ¯.¯-400 ¯.¯ ›Ç=e Ÿ=Ç” Ÿ45-96 ¯.U u›ÖnLÃ SêNõ pÆe Ÿ1400 ¯.¯-100 ¯.U vK¨< Ñ>²? ¨<eØ }ê÷M::

10. ¾SêNõ }`ÕT@

SêNõ pÆe” S¦`ÔU ¾T>‹K< u✡Ó²=›wN?` ¾¦LŸ< pÆd” c-‹ w‰ “†¨<:: /2— â?Ø 1÷20/

¾SêNõ pÆe ›Ÿóðm

SêNõ pÆe u›ÖnLÃ uG<Kƒ ÃŸðLM:: Ã¤¨<U wK<Ã Ÿ=Ç”“ ›Ç=e Ÿ=Ç” uSvM ”¨<:: Ø”ƒ ›ÃG<É KØ“ƒ“ K”vw uT>ÁS‹ G<'@***ታ*** wK<Ã Ÿ=Ç”” ÃŸóõK< 'u` pÆd” SéQõƒ c=êñ uU°^õ“ ulØ` ¾¦Ÿóðk< ›M'u\U:: eK²=I ¾Ø”ƒ ›v„‹ Ãl”'< ¯KT ¾¦d" KTÉ[Ó KØ“ƒ“ KTe***ታ***¨e ¯S^ uJ' S”ÑÉ ŸóõK¨< ›e¦LMð¨<M“M:: ›G<” uU“¾¨< G<'@***ታ*** uU°^ö‹ ¾¦Ÿóðk¨< u1228 ¯/U e,ó” K?”Ó¦” ¾¦vK ð["d© c¨< c=J” ⁕✡”Ç=G<U au`ƒ e,ó”e ¾¦vK ð["d© c¨< ulØa‹ ŸóõKA u1551 ¯/U ›d¦S¨<::

6. ትዉፊት ፤

የቃሉ ትርጉም ቅብብል ማለት ነዉ። ይኸዉም አንድ ታምኖበትና ተጠብቆ የቆየን ነገር ማስረከብና መቀበል ማለት ነዉ። አንድ ትዉልድ ጠብቆ ያቆየዉን እምነት ሲሰጥ ወይም ሲያስረክብ ሌላኛዉ ትዉልድ ደግሞ ይቀበላል። መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በጽሁፍ የሰፈረ ሰነድ አልሰጣቸዉም ይልቁንም እነርሱ እንዲቀበሉትና እንዲከተሉት በልባቸዉ ጥልቅ ዉስጥ ያኖሩት ዘንድ አዘጋጃቸዉ።

ስለዚህ ትውፊት ትናንትን ወይም ያለፈዉን ዘመን ከሁሉም ገጽታ አኳያ ለዛሬ ህያዉ አድርጎ ያቀየ፤ዛሬንም ሳይዛነፍና ሳይዛባ ለነገ የሚያሸጋግር የቤተክርስቲያን አንዱ ህይወትና የማያቋርጥ ህያዉ ምንጭ ነዉ።

ትዉፊትን ቃላዊ እንደሆነ ብቻ አድርገዉ የሚፈርጁ አነዳነድ ሰዎች ቢኖሩም ትዉፊት ግን የጽሁፍ መልክም ሊይዝ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፤በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡15 ‹‹እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥ **በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን** የተማራችሁትን ወግ (ትዉፊት) ያዙ።›› እንዳለ ቅዱስ ጳዉሎስ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ እንዴት እንደተጀመሩና መጨረሻቸዉም ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቁ በርካታ ታሪኮች በትዉፊት ተሟልተዉ እናገኛቸዋለን። ለአብነት ያህልም፦

- አሪት ዘጸአት 4፡10 ሙሴም እግዚአብሔርን፦ ጌታ ሆይ፥ እኔ አፌ ኩልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ.. ፤ይላል ሙሴ ኮልታፋ ለምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አያብራራዉም ነገር ግን በትዉፊት ለምን እንደነበር ተገልፆ እናገኘዋለን።
- የማቴዎስ ወንጌል 23:35‹‹ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ።›› ይላል የዘካርያስ ደም ግን እንዴትና በምን ምክንያት እነደፈሰሰ በትዉፊት ተዘርዝሮ እናገኘዋለን።

7. **ዲድስቅልያ፤**

- በዚህ መጽሐፍ ሐዋርያት በኢየሩሣሌም በነበሩ ጊዜ የሰሩትን ፣ የደረሠባቸውን ግፍና መከራ ፣ ተጋድሎአቸውንና የአኗኗራቸውን ሁኔታ ወዘተ የምናገኝበት መጽሐፍ ነው።

8. **<u>ሲኖዶስ ፣</u>**

ሲኖዶስ ማለት ጉባኤ ማለት ነው። ይኸውም አባቶቻችን ሐዋርያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በኋላ በ10ኛው ቀን በጽርሐ ጽዬን መንፈስ ቅዱስ ከወረደላቸው በኋላ በጋራ ተቀምጠው የሰሩት የቤተ ርክስቲያን የሥርዓት ድንጋጌዎችን የያዘ መጽሐፍ ነው። ይህ የሐዋርያት ድንጋጌ የተለያዩ አንቀጾች ያሉት በ4 የተከፈለ መጽሐፍ ሲሆን ከሰማንያ አሐዱ መጻህፍት ገብቶ የሚቆጠር አንድ መጽሐፍ ነው። ክፍፍሎቹም ፦

1. ሥርዐተ ጽዮን /ልዩ ምልክቱ ዓይን/ - 30 አንቀጽ አለው።
2. አብጥሊስ /ልዩ ምልክቱ ረስጥአ/ - 83 አንቀጽ አለው
3. ግጽው /ልዩ ምልክቱ ረስጠብ/ - 74 አንቀጽ አለው።
4. ትዕዛዝ /ልዩ ምልክቱ ረስጠጅ/ - 56 አንቀጽ አለው።

በአጠቃላይ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዛሬ ቤተርክስቲያናችን የምትቀጠምበት ልዩ ልዩ የቤተክርስቲያን ስርዓቶች በዝርዝር ተጽፈዉበት ይገኛል። ለአብነት ያህል የጾም ሥርዓት ፣ የፀሎት ሥርዓት ፣ የካህናት አባቶች የሹመት አሿሿም ሥርዓት ወዘተ ይገኝበታል።

❖ **ፍትሐ ነገሥት፤**

ይህ መጽሐፍ በውስጡ ፍትህ ሥጋዊና ፍትህ መንፈሳዊን የያዘ ነው። መጽሐፍ በሲኖዶስና በዲድስቅልያ መጽሐፍ መሠረትነት የተዘጋጀ ነው። በመጽሐፉ የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሥርዓቶችን/ህጎችን ብቻ ሳይሆን አለም የሚተዳደርበት የቤተመንግስት ህግም ይገኝበታል።

6. ሥነ ፍጥረት፤

ልዑል እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን፡ እንዲሁም በእነርሱ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ **ከምንም ወይም ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣበትን/የፈጠረበትን** ያፈጣጠር ታሪክ በዝርዝር የሚያስረዳው ክፍል ሥነ ፍጥረት ይባላል።መፍጠር የእግዚአብሔር ሥራ ብቻ ሲሆን በዘመናችን የምንመለከታቸዉ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ሥራዎችም እግዚአብሔር አምላክ ቀደም ሲል የፈጠራቸዉን ልዩ ልዩ ነገሮች በማቀናጀት የተገኙ አንጅ በዚህ ዓለም ቀደም ሲል ያልነበሩ አዲስ ፍጥረት አይባሉም፤ ጠቢቡ ሰሎሞንም እንዲህ ነበር ያለዉ፡-

- ‹‹ የሆነው ነገር እርሱ የሚሆን ነው፥ የተደረገውም ነገር እርሱ የሚደረግ ነው ከፀሐይም በታች አዲስ ነገር የለም።›› መጽሐፈ መክብብ 1:9

የዕለታት ሲያሜ ፤

የዕለታት ሲያሜ በእግዚአብሔር የተሰጠ አይደለም፤በኋላ የተነሱ ሊቃዉንት ከቋንቋና እለታቱ ከያዙት ምስጢር አንጻር እንዲጠሩበት ሰይመዋቸዋል፤

1. እሁድ ፤ የግዕዝ ቃል ነዉ ትርጉሙም አንድ ማለት ነዉ። እግዚአብሔር ፍጥረትን አንድ ብሎ የጀመረበት ቀን ነዉ።
2. ሰኞ፤ ትርጉሙ ሰነየ (መልካም አደረገ) ማለት ነዉ። እግዚአብሔር በመጀመሪያዉ ቀን የፈጠራቸዉ ፍጥረታት መልካም መሆናቸዉን እንደተናገረ፤
3. ማክሰኞ፤ ሰኞ ማግስት ማለት ነዉ።(ፍጥረት ከተጀመረ 3ኛ ቀን)
4. ረቡዕ፤ ራብዕ፤አራተኛ ማለት ሲሆን(ለፍጥረት አራተኛ ቀን ነዉና)
5. ሐሙስ፤ ሐምስ - አምስት አደረገ (ለፍጥረት 5ኛ ቀን ነዉና)
6. ዓርብ ፤ ምስጢራዊ አፈታቱ የፍጥረታት መካተቻ ማለት ነዉ፤ ፍጥረታትን ሁሉ ሲፈጥር ቆይቶ በዚህ ቀን የመጨረሻዎቹን ፍጥረታት ፈጥሮ ጨርሶአል።
7. ቅዳሜ፤ ቀዳሚት ሰንበት፤የመጀመሪያይቱ ሰንበት ስትሆን የአይሁድ ሰንበትም ትባላለች።

የፍጥረቱ ዝርዝር በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሣ ሁሉንም ለመዘርዘር የማይቻል ቢሆንም በአጠቃላይ መልኩ በሚቀርብበት ጊዜ ግን በአራት ዘፍጥረት ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ በተገለጠዉ መሰረት እንደሚከተለዉ እንመለከታለን፡-

1. እግዚአብሔር **በመጀመሪያው ቀን**) ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፤(ዘፍ.1፡1)
   /ሰባቱ ሰማያት፤ ጨለማ፤ መላእክት፤ ብርሃን፤ መሬት፤ ውሃ፤ እሳት፤ ንፋስ/ 8

2. **በሁለተኛው ቀን** ከበላይና ከበታች ያለውን ውሃ የሚለይ ጠፈርን ፈጠረ፥ ጠፈሩንም ሰማይ ብሎ ጠራው።(ዘፍ.1፡8)/ ጠፈር/ 9
3. **በሦስተኛው ቀን** ከሰማይ በታች ያለው ውሃ ተከማችቶ **ባሕር** እንዲባልና ውሃው አንድ ቦታ ሲከማች የተገለጸው ደረቅ ቦታ ደግሞ ምድር እንዲባል ወሰኖ **ዘርና ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችና ሣሮች** በምድር ላይ እንዲበቅሉ አዘዘ።እንዲሁም ሆነ።(ዘፍ.1፡13) / እፀዋት፤ አትክልት፤ አዝዕርት / 12
4. **በአራተኛው ቀን** ዕለታትን፥ሳምንቶችን፥ወሮችንና ዓመቶችን እንዲለዩ ተብሎ **ፀሐይ፥ጨረቃና ከዋክብት** ተፈጠሩ።(ዘፍ.1፡19) / ፀሐይ፥ጨረቃና ከዋክብት/ 15
5. **በአምስተኛው ቀን** <u>አዕዋፍና የባሕር ውሰጥ ተንቀሳቃሾች</u>፥ እንዲሁም ዓሣዎች ተፈጠሩ። (ዘፍ.1፡23) /በክንፍ የሚዋኙ፤ በእግር የሚጓዙ (የሚሸከረከሩ)፤ በልብ የሚሳቡ/ 18
6. **በስድስተኛው ቀን** አራዊት፥እንሰሳ /በክንፍ የሚበሩ፤ በእግር የሚጓዙ (የሚሸከረከሩ)፤ በልብ የሚሳቡትና ሰው ተፈጠሩ።(ዘፍ.1፡31) 22

የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረቶች ሁሉ እግዚአብሔር በቃሉ እንደፈጠራቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ።አፈጣጠሩም ከምንም ነው እንጅ የሰው ልጆች አንድን ነገር ለመፈልሰፍ አንዱን ንጥረ ነገር በማሻሻል ወይም አንዱን ከሌላው ጋር በማቀላቀል የሚያከናውኑት ዓይነት ሥራ አይደለም።ስለዚህ ነው ነቢዩ ዳዊት ‹‹በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተፈጠሩ፤የሰማይ ሠራዊትም ሁሉ በአፉ አስትንፋስ… እርሱ ስለተናገረ ሆነዋል፤እርሱም ስላዘዘ ጸንተዋልና›› ያለው።/መዝ.33 ቁ.6-9/

እንዲሁም ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.11 ቁ. 3 ‹‹ዓለም በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ የምናውቀው በእምነት ነው፤የምናየው ነገር ሁሉ ከምንም እንደተገኘ በእምነት እናስተውላለን›› ተብሏል።

<u>የሰው አፈጣጠር፤</u>

- **እግዚአብሔር አምላክ ለሰው አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ፈጥሮ ካዘጋጀለት በኃላ በመጨረሻ በስድስተኛው ቀን ‹‹ሰውን በመልካችንና እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" አለ››/ዘፍ.ም.1 ቁ. 26/**
- **የሰው አፈጣጠር ከሌላው ፍጥረት ሁሉ የተለየ የሆነው በእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ ግምት ስለተሰጠው ነው።እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ በፈጠረ ጊዜ ይሁን ብሎ በቃሉ እያዘዘ ከመሆናቸው ማለትም ከመፈጠራቸው በቀር ሌላ የተለየ አድራጎትን አላደረገም።ሰውን ከመፍጠሩ በፊት ግን ከላይ እንደተገለጸው በምን ዓይነት እንደሚፈጥረው መለኮታዊ ዕቅድ ከማውጣቱም በላይ በኦሪት ዘፍጥረት ም.2 ቁ 7 ላይ ለሰው ልጅ የማትሞት ነፍስን በመስጠት እንዳከበረው ተነግሮናል።**
- **ኦሪት ዘፍጥረት 2፡7‹‹ እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።››**

- **እንዲሁም እግዚአብሔር አምላክ ከቀድሞ ጀምሮ ለሰው ልጅ የሚበጀውን ነገር ሁሉ በማዘጋጀት ኑሮውን ያመቻችለት የነበረ በመሆኑ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለምና አብሮት የሚኖር ረዳት እንፍጠርለት ብሎ ከጉኑ አጥንት በመውሰድ ሔዋንን ፈጠረለት።/ዘፍ. ም. 2 ቁ 18-25/**
- **አዳምም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ የተባለው በጽድቅ፣በቅድስናና በሕያውነት ነበር።በትእዛዘ አፍራሽነቱ ግን ሕያው ከመሆን ሟች ሆኗል፤ጽድቅና ቅድስናውንም በጎጠአተኛነቱ ምክንያት እንዲያጣቸው ተደርጓል።**
- **እግዚአብሔር አምላክ ሰዉን ከሰባት ባህርያት ፈጥሮታል ስለዚህም ሰዉ ተባለ።እነዚህም 3ቱ የነፍስ ባህርያት(ለባዊት፤ነባቢት፤ህያዊት) ፤4ቱ የስጋ ባህርያት ደግሞ(ነፋስ፤እሳት፤ዉሃና መሬት ናቸዉ)።እነኝህ ባህርያት በሰዉ ልጅ ዉስጥ ይኖራሉ።**

<u>የመላእክት አፈጣጠር</u>

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ በሚልበት ጊዜ ሰማይ ከምድር በፊት መጠቀሱ ሰማይና በሰማይ የሚገኙ መናፍስት ከምድር በፊት ስለተፈጠሩ ነው።ይህን አባባል ሲያጠናክር ነቢዩ ዳዊት ‹‹በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተፈጠሩ፤ የሰማይ ሠራዊትም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ›› ብሏል።/መዝ. 33.6/ ስለዚህ መላዕክት የመጀመሪያዉ ቀን ፍጥረቶች ናቸዉ።መላእክት የተፈጠረት በመጀመሪያው ቀን መሆኑን በመጽሐፈ ኩፋሌ 2.6-8 ተገልጾልል፤

መላክትም መናፍስት ናቸው።እነዚህም መናፍስት በሁለት ክፍል ይከፈላሉ።የመጀመሪያዎቹ ክፍሎች ቅዱሳን፣ሁለተኛዎቹ ክፍሎች ደግሞ ርኩሳን የሚል ቅጽል ስም አላቸው።

<u>ብዛታቸዉ፤</u>

ሐዋርያው ዩሐንስ በራእይ መጽሐፉ ም.5 ቁ.11 ላይ ስለ መላአክት ብዛት ሲገልጽ እንዲህ ብሏል።

‹‹አየሁም፣ በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም አእላፋት ጊዜ አእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር።››

<u>የመላዕክት አለቃ፤</u>

የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ መላአክት አለቃ እንዳላቸው ይገልጣሉ።ለዚህ እምነት መሠረት የሆኑት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- **‹‹በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል።›› /ዳን.ም.12 ቁ. 1/**
- **‹‹ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ።›› /ዳን.ም.10.ቁ.13/**
- **‹‹የመላአክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም።››/ይሁ1፤9/**

- ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ የሚለውን ጥቅስ መሠረት በማድረግ ሌሎችም አለቆች አሉ እንጂ ሚካኤል ብቻውን የመላእክት አለቃ አይደለም።

<u>የሰይጣን ዉድቀት፤</u>

የሰይጣን አፈጣጠር ከመላእክት አንደ አንዱ የነበረ ቢሆንም በትዕቢት ኀጢአት በመውደቁ ከክብሩ የተዋረደ መሆኑን ሲያመለክት ኢሳይያስ በትንቢቱ እንዲህ ብሎ ገልጾታል።

‹‹አንተ የንጋት ልጅ አጠቢያ ኮከብ ሆይ፥እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? አሕዛብን ያዋረድህ አንተ ሆይ፥እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቁረጥህ? አንተን በልብህ .ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፤ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፤በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ከዳምናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፤በልዑልም እመሰላለሁ አልኸ።ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጉድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ።››ኢሳ.ም.14 ቁ.12-15/

ከዚህ ዉድቀቱ በኋላ ሰይጣን ለሰዉ ልጆች ጠላት ሆኖ በብዙ የተንኮል ስራዎች ሰዎችን ከእግዚአብሔር መንግስት እያራቀ ይገኛል፡-

- በእባብ ውስጥ ሆኖ የመጀመሪያይቱን የሰው ልጆች እናት በማሳሳት አዳምና ሔዋን ቦኀጢአት እንዲወድቁ አድርጓል።/ዘፍ.ም.3 ቁ.1-2/

- ሰይጣን በእስራኤል ላይ ተነሥቶ ሕዝቡን ይቁጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው። /1ኛ ዜና.ም.21 ቁ.1/
- ታላቁ ካህን ኢያሱን ይከሰሰው ዘንድ ሰይጣን በስተቀኙ ቆሞ ነበር።/ዘካ.ም.3 ቁ.1/

ዋቢ መጻህፍት፤

- ትምህርተ መለኮት
- ኮኮሐ ሐይማኖት
- ሥነ ፍጥረት
- የተለያዩ አድባራት ሰ/ት/ቤቶች የተከታታይ ኮርስ ማንዋሎች

ይቆየን